# የተሻሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ

## ረቂቅ ሰነድ

ጥቅምት 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መልእክት

# የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መልእክት





# ማውጫ


መግቢያ ..... 1

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት ..... 1

1. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻዎችና ልምዶች ..... 2

1.1 ሃገር ግንባታ ..... 3

1.2 ሃገራዊ ክብር ..... 3

1.3 የዜጐች መብት እና ደህንነት ማስጠበቅ ..... 5

1.4 ቀጠናዊ የጂኦፖለቲካ ሁኔታ እና ቀጠናዊ ውህደት ..... 5

1.5 አለም አቀፋዊ ሁኔታና አዝማሚያዎች ..... 6

2. መርሆዎችና እሴቶች ..... 7

2.1 መርሆዎች ..... 7

2.2 እሴቶች ..... 7

3. ዓላማዎች ..... 8

4. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ስትራቴጂዎች ..... 11

4.1 የሰላም ዲፕሎማሲ ..... 11

4.1.1 የዓለም አቀፍ ሰላምና ደህንነት ..... 11

4.1.2 ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ..... 11

4.1.3 ሰላም ማስከበርና ስምሪት ..... 12

4.2 የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ..... 13

4.2.1 ዓለምአቀፍ ንግድን ማስፋፋት ..... 13

4.2.2 ቴክኖሎጂ ሽግግርና የሳይንስ ዲፕሎማሲ ..... 13

4.2.3 ኢንቨስትመንት ..... 14

4.2.4 የልማትና የኢኮኖሚ ትብብሮች ........ 15
4.2.5 ቱሪዝም ........ 16
4.2.6 የወደብ አገልግሎትና የማሪታይም ጉዳዮች ........ 16
4.3 ዜጋ-ተኮር ዲፕሎማሲ ........ 18
4.4 ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ........ 19
4.4.1 ሚዲያ ........ 20
4.4.2 ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶች ........ 20
4.4.3 ህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችና ጉድኝቶች ........ 21
5. ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ........ 22
5.1 የአየር ንብረት ለውጥ ........ 22
5.2 ፍልሰትና ስደተኝነት ........ 22
5.3 ዘላቂ ልማት ........ 23
5.4 የሳይበር ቴክኖሎጂ ........ 23
5.5 የጠፈር ሳይንስ ጉዳይ ........ 24
5.5 ተፈጥሮ ሀብትና ኢነርጂ ........ 25
5.6 ሰብአዊ ጉዳዮች ........ 25
6. ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም-አቀፋዊ ግንኙነቶች ........ 26
6.1 ጐረቤት አገሮች ........ 26
6.1.1 የፖለቲካ ጉዳዮችና ዓለም አቀፍ መድረኮች ........ 26
6.1.2 አካባቢ ደህንነትና ሰላምን ማረጋገጥ ........ 27
6.1.3 ኢኮኖሚያዊ ትስስር ........ 27
6.1.4 የህዝብ ለህዝብ ትስስርና ግንኙነት ........ 29

6.1.5 የወደብ አገልግሎት ........................................................................ 29
6.1.6 የድንበር አከባቢዎች እና ድንበር-ተሻጋሪ የተፈጥሮ ሀብቶች ......................... 30
6.2 ታላላቅ ሀይቆች አካባቢ........................................................................ 31
6.3 ድንበር ተሻጋሪ ሀብቶችና የአባይ ተፋሰስ ................................................ 31
6.3 የአፍሪካ ሀገራትና አፍሪካ ህብረት .......................................................... 32
6.3.1 የአፍሪካ አገራት ............................................................................ 32
6.3.2 የአፍሪካ ሕብረት ............................................................................ 34
6.4 መካከለኛው ምስራቅ ............................................................................ 36
6.5 የአውሮፓ ህብረት ............................................................................ 37
6.5.1 ኢኮኖሚ ትብብር ............................................................................ 37
6.5.2 ፍልሰትና ስደተኝነት ........................................................................ 38
6.5.3 በሰላምና ፀጥታ መስክ መተባበር .......................................................... 39
6.6 የአውሮፓ ሃገራት ............................................................................ 39
6.6.1 ንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ....................................................... 39
6.6.2 ሰላምና ደህንነት ............................................................................ 40
6.6.3 ዓለምአቀፍ ጉዳዮች.......................................................................... 40
6.7 የሰሜንና ደቡብ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች ........................................... 41
6.7.1 ሰሜን አሜሪካ................................................................................ 41
6.7.2 የደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን አገሮች ..................................................... 42
6.8 እስያ-ፓስፊክ ................................................................................ 43
6.9 የባለ-ብዙ ወገን ግንኙነቶች .................................................................. 44
7. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አፈፃፀም ........................................................... 46

7.1 አቅጣጫና አካሄድ ........................................................................ 46

7.2 ተቋማዊ አሰራር ........................................................................ 46

7.3 የፖሊሲ ጥናትና ትንተና ........................................................................ 47

7.4 ሥልጠና እና የአቅም ግንባታ ........................................................................ 48

# መግቢያ

## የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት

የቀድሞው የውጭ ጉዳይና ሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራተጂ በሚቀረፅበት ወቅት ታሳቢ ያደረጋቸው ሃገራዊ፣ ክልላዊ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ባለፉት ሃያ አመታት በብዙ መልኩ የተቀየሩ መሆናቸውን ነው። ኢትዮጵያ ከሃያ አመት በፊት ወደ ስልሳ ሚልዮን ገደማ የሚገመት ህዝብ እና ከ10 ቢልዮን ዶላር የማይበልጥ አጠቃላይ አመታዊ ምርት የነበራት ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ከመቶ ሚልዮን በላይ የሚገመት ህዝብና መቶ ቢሊዮኖች ዶላር በላይ የሚገመት አጠቃላይ አመታዊ ምርት ባለቤት ነች። ይህም የራሱን መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮቶች ማስከተሉ አይቀርም። በማህበራዊ ጉዳዮች ረገድ መጠነ-ሰፊ ለውጥ የታየ ሲሆን በመሰረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ፣ ጤና፣ ትምህርት ወዘተ ዘርፈ-ብዙ ስኬት ተመዝግቧል። በፖለቲካው መስክ ደግሞ መጠነ-ሰፊ የዲሞክራሲ ማሻሻያ ምህዳር ተዘርግቶ ሀገሪቱ ዘላቂ እና አስተማማኝ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የምትገነባበት መልካም አጋጣሚ ተፈጥሯል። ይህንን የተሻሻለውን የውጭ ፖሊሲ ሰነድ እነዚህን እና ሌሎች ሃገራዊ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መከለስ አስፈላጊ አድርጎታል።

ሀገሪቱ የምትገኝበት ቀጠና ሁኔታም በብዙ መልኩ እየተቀያየረ ይገኛል። የቀድሞው ሀገራዊ የውጭ ጉዳይና ደህንነት ፖሊሲ እና ስትራተጂ በተቀረፀበት ወቅት ደቡብ ሱዳን የምትባል ሃገር ያልነበረች፣ ከኤርትራ ጋር መልካም ግንኙነት ያልነበረበት፣ ሶማሊያ መንግስተ አልባ የሆነችበት ሁኔታዎች የነበሩ ሲሆን አጠቃላይ ቀጠናዊ ጂኦፖለቲካውም ከዚህ የማይተናነሱ ሌሎች አዳዲስ ክስተቶች እና አዝማሚያዎችን ሲያስተናግድ ቆይቷል። ከሞላ ጎደል ሰላምና ደህንነት ሰፍኖበት የነበረው የቀይ ባህር እና የኤደን ባህረሰላጤም ከማንኛውም ጊዜ በላይ ፍጥጫ እና አደጋ ተደቅኖበታል።

በተመሳሳይም አለም-አቀፋዊ ስርዓቱ መጠነ ሰፊ ለውጦችን አስተናግዶ፣ የጨዋታው ህግ በተለያየ መልኩ እየተቀያየረ በመምጣቱ መጠነ-ሰፊ በሆነ መልኩ እና መገመት በማይቻል ሁኔታ አጠቃላይ የስርዓት እና የሃይል ሚዛን ሽግሽግ እየተካሄደ ይገኛል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እና ስትራተጂ እነዚህን ለውጦች እና አዝማሚያዎች እንዲሁም ቀጣይ ለውጦችን ባገናዘበ መልኩ መከለስ እንደሚኖርበት በማመን ይህ የፖሊሲ ክለሳ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ተከናውኗል።

# 1.የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻዎችና ልምዶች

የአንድ ሃገር መሰረታዊ ብሄራዊ ጥቅም ተብሎ የሚወሰደው ሃገራዊ ህልውናን፣ ሉአላዊነትን፣ አንድነትን፣ ደህንነትን እና ክብር ማስጠበቅ፣ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማረጋገጥ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሰረታዊ ማጠንጠኛው ሃገራዊ ህልውናን እና ደህንነትን ማስጠበቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ዋና ዋና ጉዳዮች እና አላማዎች መኖራቸው የማይቀር ቢሆንም ከህልውና የሚቀድም ጉዳይ ስለሌለ ይህንን ማረጋገጥ ዋና እና መሰረታዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ይሆናል።

ሃገራዊ ህልውናን እና ደህንነትን ማስጠበቅም ሆነ ከዚህ ቀጥሎ የተቀመጡትን ጉዳዮች እና አላማዎችን ለማሳካት የሚያስችል የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በሚቀረፅበት ወቅት እንደ መነሻ ሊወሰዳቸው የሚገቡ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች መለየት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ነባራዊ የዓለም ሁኔታ በእጅጉ እየተቀየረ የመጣ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ ከጐረቤቶቿ ጋር ያላትን ግንኙነቶች እየተሻሻለና እየጠነከረ በመምጣቱ ይህንን ተከትሎ የሚቀየሩ መነሻዎች መኖራቸው የማይቀር ነው።

ኢትዮጵያ ዘመናዊ መንግስት አቋቁማ የውጭ ግንኙነት ፓሊሲዋን ማራመድ ከጀመረችበት ወቅት ጀምሮ በቋሚነት የማይለወጡ ጉዳዮች የመኖራቸውን ያህል እንደሁኔታው በየጊዜው እየተቀያየሩ ነባራዊውን የፓለቲካና ኢኮኖሚ ሁኔታ ያገናዘቡ ለውጦች መኖራቸው አልቀረም። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሃገሪቱ የውጭ ግንኙነትና ሃገራዊ ደህንነት ፓሊሲ በ1994 ዓ.ም. ከወጣበት ግዜ ጀምሮ የተከሰቱትን አዳዲስ አዝማሚያዎች እና በቋሚነት የቆዩ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ የተሻሻለው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የሚከተሉትን አምስት ዋና ዋና ጉዳዮች እና አዝማሚያዎችን በመነሻነት በመውሰድ ተዘጋጅቷል።

## 1.1 ሃገር ግንባታ

የሃገራዊ ግንባታ ራዕይ መልኩን እና ባህሪውን ሊቀይር የሚችል ቢሆንም በየትኛውም ጊዜ የማያቋርጥ እና ተከታታይ ስራ የሚጠይቅ ስለሆነ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ዋና መነሻ ሆኖ ይቀጥላል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የተቀመጠው የጋራ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ የመገንባት ራዕይ ገና ያልተጠናቀቀ ተግባር በመሆኑ ይህንን ለማሳካት የሚያስችሉ ሰላምና ደህንነትን ማስጠበቅ፣ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ተግባራትን ያለመታከት ማከናወን፣ ፈጣን እና ዘላቂነት ያለው ልማት ማረጋገጥ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማስፈን ፖሊሲው እንደ መነሻ የሚወስደውቸው ቀዳሚ ጉዳዮች ሆኖው ይቀጥላሉ።

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ውጤታማ እንዲሆን ባለፉት አመታት በሀገሪቱ የተመዘገቡትን ውጤቶች አጠናክሮ ማስቀጠል አስፈላጊ ነው። ለዚህም ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን፣ የዲሞክራሲያዊ ስርዓትን መገንባት ፣ መልካም አስተዳደርን ተግበራዊ ማድረግ ፣ ሰብአዊ መብትን ማክበርና ማስከበር እና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን ማረጋገጥ አሁንም ትኩረት የሚሹ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም በብሄራዊ መግባባትና በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ የዳበረ የፖለቲካ ስርዓት እና የህገ-መንግስታዊና አስተዳዳራዊ ተቋማት መጠናከር ለሚያግዙ ጥረቶች ድጋፎች የሚያስገኝ ዲፕሎማሲን በጥብቅ መከተል ያስፈልጋል።እነዚህን ዋና ዋና ጉዳዮች መሰረት ያደረገ ሃገራዊ ግንባታን ማረጋገጥ በመሆኑ በሃገር ውስጥ ጥንካሬ እና ተግዳሮቶች ላይ ያተኮረ እና በዋናነት ኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲን የሚያራምድ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መከተል መነሻ ሆኖ ተወስዷል።

## 1.2 ሃገራዊ ክብር

ሃገራዊ ክብር እና ኩራትን ማስጠበቅና ማራመድ የብዙ ሃገራት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻ ተደርጎ ሲተገበር ቆይቷል። የአንድ ሃገር ብሄራዊ ማንነት በታሪክ፣ በተመዘገቡ ድሎች እና በተከሰቱ ብሄራዊ ችግሮች በአመዛኙ የሚወሰን በመሆኑ ብሄራዊ ማንነትን ለበለጠ ስኬት እና የተሻለ ሃገር ለመገንባት ሲጠቀሙበት ይታያል።

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ እና የቀደምት ስልጣኔዎች ባለቤት፣ በቅኝ ያልተገዛች አፍሪካዊት ሃገር፣ የተለያዩ የእምነት ተከታዮች በመከባበር የሚኖሩባት ሃገር፣ እንዲሁም የተለያዩ ቋንቋዎች፣

ሃይማኖቶች እና ባህሎች ያላቸው ህዝቦች አብረው ለዘመናት የኖሩባት ሃገር መሆኗ የኩራት ምንጮቿ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳሉ። ሀገሪቱ ለዘመናት ከተላበሰችው የሚያኮሩ ታሪኮች፣ ድሎች እና ባህሎች በተጨማሪ ቀደም ብሎ በአሉታዊ መልኩ ትታወቅበት የነበረውን ድህነት በመጠኑም ቢሆን እየቀረፉ የሚገኙ የልማት ስኬቶች መመዝገባቸው፣ እንዲሁም ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ መንግስት የጀመረው መጠነ-ሰፊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማሻሻያና የለውጥ ጅማሮዎች መታየታቸው በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም እስከአሁን የተመዘገቡትን ውጤቶች እንደ መነሻና ማስፈንጠሪያ በመጠቀም አሁንም የሚታዩትን እና ያሉብንን ክፍተቶች በመሙላት ወደ ላቀ የእድገትና ስልጣኔ ደረጃ የመሸጋገር አስፈላጊነት የፖሊሲው መነሻ ሆኖ ይቀጥላል።

አንዳንድ የእስያ ሃገራት በተለያየ ወቅት የስልጣኔ ባለቤት የነበሩ ቢሆኑም በ19ኛው እና 20ኛው ክፍለ ዘመን ግን ወደ ኋላ ቀርተው እንደነበር ይታወቃል። ነገር ግን የቀደምት ስልጣኔያቸውንና አገራዊ ኩራት መነሻ በማድረግ እና ወደ ኋላ መቅረታቸውን ደግሞ እንደ ቁጭት ተነሳሽነት በመጠቀም በዓለም መድረክ ላይ እንደገና ገናናነት እና ሃያልነት መጎናፀፋቸው እንዲሁም የስልጣኔ መሠረታቸውንና ብሄራዊ ማንነታቸውን እና ባህላቸውን ሳይቀይሩ ማሳካታቸው እንደ ተመክሮ የሚወሰድ ነው። ይህ ማለት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው የእነዚህን ሃገራት ተሞክሮ ሙሉ ለሙሉ እንደ መነሻነት ይወስዳል ማለት ሳይሆን በጎ ተሞክሯቸውን እና ከሃገራችን ጋር የሚያመሳስላቸውን ጉዳዮች በመምረጥ ለሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ በሚጣጣም መልኩ በመቅሰም እና የሚታዩ ጉድለቶችን በማስተካከል የተሻለች ሃገር ለመፍጠር መስራት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ብሄራዊ ኩራትን እንደ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻ መውሰድ ይገባል።

## 1.3 የዜጐች መብት እና ደህንነት ማስጠበቅ

የዜጎችን መብት፣ ክብር እና ጥቅም መጠበቅ እና ማስጠበቅ የአንድ ሃገር መንግስት ሀላፊነት መሆኑ እሙን ነው። ይህ በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሃገር የሚገኙ ዜጎችንም የሚያካትት ይሆናል። በመሆኑም ዜጋ-ተኮር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እና የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ማካሄድ አንዱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል። በዚህም ዜጐች በአገራቸው ጉዳይ ላይ ባለድርሻ እንዲሆኑና በየሚኖሩበት ሃገር የኢትዮጵያ ገፅታ ገንቢ አምባሳደሮች ሆነው እንዲያገለግሉ ማበረታታት ከግምት ውስጥ ገብቷል። በመሆኑም ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል ያደረገ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመገንባት እና ብሂራዊ መግባባትን ለማምጣት የሚያስችል ውስጣዊ እና ውጫዊ አስቻይ ሁኔታዎች መፍጠር፣ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች በሚኖሩበት ሃገር መብታቸው እና ጥቅማቸው እንዲከበር መስራት አንዱ የፖሊሲው መነሻ ነው።

በሌላ መልኩ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ከሃገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር እንዲያጠናክሩ፣ በትውልድ አገራቸው ህግ የሚፈቅድላቸው ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከሚገኙ እድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተጀመሩትን የሕግ አግባቦች ማጠናከር ያስፈልጋል።

## 1.4 ቀጠናዊ የጂኦፖለቲካ ሁኔታ እና ቀጠናዊ ውህደት

በቀጠናችን በቅርብ አመታት ወዲህ የተከሰቱ ጂኦፖለቲካዊ ለውጦች እና በቀይ ባህር ዙርያ ያለው ሁኔታ እና የሃይል አሰላለፍ የባህርበር ለሌላት ኢትዮጵያ እና በአጠቃላይ ለቀጠናው ደህንነት ከፍተኛ አንደምታ እንደሚኖራቸው ግልፅ በመሆኑም በቀጠናው ዙሪያ የሚታየው ለውጥ የሀገሪቱን ደህንነት እና ብሂራዊ ጥቅም ስጋት ላይ እንዳይጥል ዘላቂነት ያለው ፈጣን የወደብ አገልግሎት የማግኘት እድሏን ለማረጋገጥ በትጋት መስራት ያስፈልጋል። በመሆኑም ቀጠናዊ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታው አንዱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው መነሻ ሆኖ ይቀጥላል። በተጨማሪም፣ በቀጠናው እና በአፍሪካ ለማምጣት የሚታሰበው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ውህደት እና ትስስር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ በበኩሉ ለፖሊሲው መሳካት እና በቀጠናው እና በአለም አቀፍ ደረጃ እየታዩ ላሉ ክስተቶች እና አዝማሚያዎች የጋራ እና የተቀናጀ ምላሽ ለመስጠት ጠቃሚ ነው። በመሆኑም ቀጠናዊ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ እና ክልላዊ ውህደት የሚያስከትላቸውን እድሎችና ተግዳሮቶች የፖሊሲው መነሻ አድርጎ መውሰድ ይገባል።

## 1.5 አለም አቀፋዊ ሁኔታና አዝማሚያዎች

አሁን የምንገኝበት ወቅት አለማቀፋዊ የሽግግር ወቅት በመሆኑ በአለማችን እየተከሰተ ያለው አለም አቀፍ የሃይል አሰላለፍ በርካታ ለውጦች ይስተዋሉበታል። በአንድ በኩል አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሚዛኑ ከምዕራቡ አለም ወደ ምስራቁ አለም እየተሸጋገረ በመሄድ ላይ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሚዛኑም በአንድ ሃይል ስር የተከማቸ ከመሆን አልፎ ወደ የተለያዩ የኢኮኖሚ ሃይሎች ተፅእኖ ሥር የተሸጋገረበት ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ ነው። ከእነዚህ ሁለት አውታሮች በተጨማሪም በሃገሮች መንግስታት የበላይነት ተይዞ የቆየው አጠቃላይ ሂደት እየተለወጠ መንግስታዊ-ያልሆኑ ሃይሎች/ተዋንያን የተለያዩ አቅሞች እያገኙና እያዳበሩ የሚገኙበት ሁኔታ ይስተዋላል።

አሁን ያለው አለማቀፋዊ የግንኙነት ስርዓት በአራት ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ ለውጦች እያስከተለ በመሄድ ላይ ይገኛል።

1. ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት ወዲህ የተዘረጋው የአለምአቀፍ ስርዓቱ ዋና ተዋንያን የሆኑት ሀገራት ከተለያዩ አቅጣጫዎችና በተለይም በሀገር ውስጥ ጫና እየደረሰባቸውና አንዳንዴም የነበራቸው ተፅእኖ መዳከም ወይንም የዓለም አቀፍ ሥርዓቱን ለማስቀጠል ፍላጎት የማጣት አዝማሚያ እያሳዩ ናቸው።
2. የአለምአቀፉ የፖለቲካ ስርዓትና የኢኮኖሚ ስርዓት እርስ በርሳቸው ያልተጣጣሙበት ወቅት ላይ ደርሷል። አለም አቀፉ የኢኮኖሚ ስርዓት ከሞላ ጎደል አለማቀፋዊ (ሉላዊ) ባህሪ ይዞ ያለ ሲሆን ፖለቲካዊ ስርዓቱ ግን አሁንም በእያንዳንዱ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተና በተለይም ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ የምዕራቡን ዓለም ጨምሮ የፅንፍ የፖለቲካ ሃይሎች ወደ መንግስታዊ ሃላፊነት በምርጫ ስልጣን የያዙበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው።
3. ሃያላን ሀገራት በዋና ዋና አለማቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ የሚመካከሩበት፣ ከተቻለም የሚተባበሩበት ውጤታማ ባለብዙ-ወገን መድረክ እየተዳከመ መሆኑ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ስብስቦችና ተዋናዮች በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚጫወቱት ሚና እየጎለበተ በመምጣት ላይ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

4. ለዘመናት በጥቂ አገራት ተይዞ የነበረው የአለማቀፋዊ የአመራር ሰጪነት ሚና በአዳዲስ ዓለም አቀፋዊ ኃይሎችና በቀጠናዊና ክልላዊ ኃይሎች ቀስ በቀሰ እየተተካ መምጣቱና ሌሎች መሰል አለም አዝማሚያዎች የፖሊሲው መነሻ ተደርገው ተወስደዋል።

# 2.መርሆዎችና እሴቶች

## 2.1 መርሆዎች

1. ተገቢና ዘላቂ ጥቅም የሚያስጠብቁ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን የውጭ ግንኙነት ሥራዎችን አጠናክሮ ማካሄድ፣
2. በኢትዮጵያና በሌሎች ሃገራት በተለይ በጐረቤቶቿና የአፍሪካ ሃገራት መካከል ያለውና የሚኖረው ግንኙነት በመከባበር፣ ሉዐላዓዊነትን ባስጠበቀና መርህን በተከተለ አግባብ እንዲሁም የጋራ ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ መልኩ እንዲራመድና እንዲተገበር ማድረግ፣
3. በሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶች በገለልተኛነትና በፍትሐዊነት እንዲፈቱ ማገዝ፣
4. ሀገሪቱ ለተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍዊ፣ አህጉራዊና ክፍለ-አህጉራዊ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች መገዛት፣
5. ለሀገራት መልካም የትብብርና ሰላማዊ ግንኙነቶች ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም-አቀፍዊ ስምምነቶችና ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ በትብብር እንዲፈቱ ማድረግ፣

## 2.2 እሴቶች

ኢትዮጵያ እስከአሁን በስፋት የምትታወቅባቸው መገለጫዎች ታሳቢ በማድረግ የውጭ ግንኙነት ፓሊሲው እንደ እሴት የሚወስዳቸው የሚከተሉት ናቸው።

1. የረጅም ጊዜ የሀገራዊነትና ሉዐላዊ የነፃ መንግሥትነት ታሪክ፣
2. በርካታ ሕዝብ፣ ሠፊ ሊለማ የሚችል መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት፣
3. የበርካታ ባህሎች፣ ሀይማኖቶች፣ ቋንቋዎችና የአኗኗር ዘይቤዎች፣ መቻቻሎች፣ መስተጋብሮች፣ መወራርሶችና አብሮነቶችን የተላበሰች ሃገር መሆን፣

4. ዘላቂና ሰላማዊ የግጭት አፈታት ሀገር-በቀል ልምዶችና እሴቶች ለመጠቀም የምትጥር ሃገር መሆን፣
5. የፌዴራሊዝም መርሆዎች (የራስ ገዝና የጋራ አስተዳደር) መሠረቶችና ጅማሮዎች መኖር፣
6. የዓለም አቀፍ አህጉራዊና ቀጠናዊ ድርጅቶች መሥራች አባልና መቀመጫ መሆን፣
7. የጋራ ሰላም መርህ አራማጅ፣ ሰላም በማስከበርና ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግልን የማገዝ ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር መሆን፣፣
8. የገለልተኝነት መርህ አራማጅና በሀገራት መካከል ችግሮችንና ግጭቶችን በሰላም የመፍታት ታሪክና ልምድ ያላት ሀገር መሆን፣
9. የረጅም ጊዜ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ታሪክና ልምድ እንዲሁም የሀገራትን ሉዓላዊነት የማክበር ባህል ባለቤትነት፣
10. በቅርብና በሩቅ ከሚገኙ ሃገራትና ህዝቦች ጋር የተመሰረቱ የረጅም ጊዜ ግንኙነቶች፣
11. በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናን ያገኙና ከበሬታ የተቸራቸው የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ባህላዊ ታሪካዊና የሥልጣኔ ቅርሶች ባለቤትነት

ፖሊሲው ታሳቢ ያደረጋቸው ዋና ዋና እሴቶች ናቸው።

# 3.ዓላማዎች

የኢትዮጵያ ደህንነት ለከፋ አደጋ የሚጋለጠው፣ አገራዊ ያለመረጋጋት አደጋ የሚፈጠረው እና የተመፅዋችነት ችግር የሚጋረጠው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲሁም አሳታፊ ዴሞክራሲ እውን ሳይሆኑ ሲቀሩ በመሆኑ፣ ከውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አኳያ ዋና አላማዎቹ እነዚህን ተግዳሮቶች በመቅረፍና በመቋቋም አሉታዊ እንደምቶዎቻቸውን ማስወገድ ይሆናል። ይህን ውጤታማ ለማድረግም የተመቻቸ የውጭ ሁኔታና ግንኙነት መፍጠር የግድ ይላል።

ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥና ኢኮኖሚያዊ እድገት እውን ለማድረግ፤ ለሃገር ውስጥ ምርቶች ሰፊ የገበያ እድልን ማስገኘት፤ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ፣ የልማት ፋይናንስ ፍላጎትን የሚያግዝ የብድርና እርዳታ እንዲሁም የሳይንስና የቴክኒክ ድጋፎችን ለይቶ ማግኘት አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጓዳኝ የዳበረ ዴሞክራሲ ግንባታ በአገሪቱ እውን ለማድረግ

የሚያስችልና አሳታፊ አስተዳደርዊ ተቋሞችን ለማጠናከር ደጋፊ የሚሆን የቴክኒክና የፋይናንስ እገዛም ለማግኘት መትጋት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የዲሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ እና ህገመንግስቱን መሰረት ያደረገውና ብዝሃነትን ማስተናገድ በሚችል መልኩ የተገነባውን የፌዴራል ስርአት ለማጠናከር የሚረዱ በርካታ ስራዎችን ማከናወን ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። እነዚህ ዓላማዎች ለማሳካትም የውጭ ግንኙነት እንቅስቃሴ በዋናነት በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ የተማከለ ይሆናል።

የውጭ ግንኙነት ፓሊሲው ከውጭ የሚቃጡ አገራዊ ደህንነትና ሰላም የሚፈታተኑ ተግዳሮቶችን ከተቻለ ለማስወገድ  ካልተቻለም የመቀነስ ግብ አለው። ከዚህም አኳያ የሰላምና ደህንነትን ሁኔታ የሚያራምድ አከባቢያዊና አለምአቀፋዊ ሁኔታ እንዲሰፍን የማድረግና፣ ከዚህ በፊት የተፈጠሩ ግንኙነቶችን ይበልጥ በማጠናከር አዳዲስ አጋዥ ኃይሎችን የማበራከት ግብ አለው። ፓሊሲው በብሄራዊ ጥቅም ላይ የሚቃጡና ሊሰነዘሩት የሚችሉትን አደጋዎችን አስቀድሞ የመተንበይና ተግዳረቶች ሳይሰፉ የመፍታት አቅምን የመፍጠር አላማ አለው።  በዚህ አግባብ ሊፈቱ የማይችሉ ሁኔታዎች ከተከሰቱ ፖሊሲው በሰላማዊ መንገድ ፣ በሰከነ  አግባብ ፣ በውይይትና በድርድር እንዲፈቱ የማድረግ ግብ ይዞ የተቀረፀ ነው።

ድንበር-ተሻጋሪ የውኃ ሃብቶቻችንን በፍትሃዊ መልኩና በጋራ የመጠቀምን እድል በማጠናከር የላቀ ተጠቃሚነት  የሚያረጋግጡ ግንኙነቶች ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት የፓሊሲው አንድ አካል ነው። ፓሊሲው ለሀገሪቱ ልማት የሚያግዝ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንፃር ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ተደርጎ የተቀረፀ ነው። በተጨማሪም አህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስሮች፣ አለምአቀፋዊ ክስተቶች በተለይም የአየር ንብረት ለውጥ፣ ስደተኝነት፣ ድንበር-ዘለል የተደራጀ ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ አክራሪነትና ፅንፈኝነት፣ የሳይበር ጥቃት ወ.ዘ.ተ በልማት ፣ በሰላም እና የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ የሚፈጥሩ ተግዳሮቶች በመሁማቸው እነዚህን በግልና በጋራ ጥረት የመቀነስና የማስወገድ ግብም አለው። የሀገሪቱን ዘላቂ ሰላምና ቀጣይነት ያለው ልማት ከማረጋገጥ አንፃር በቀጠናው የተጀመሩ የኢኮኖሚ ትብብርሮች እና ትስስሮችን በማጠናከር በተለይም የጋራ ሃብቶችን በጋራ የማልማትና የመጠቀም አቅጣጫን የከተላል። ይህም  የዲፕሎማሲው እንቅስቃሴ ዋነኛ ማዕከል እንዲሆን የሚያደርግ ተጨማሪ ምክንያት ነው።

በቀጠናው ፣ በአህጉርና በአለምአቀፍ ደረጃ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት፣ ሰላምና ደህንነትን የማስጠበቅ ተልእኮዎችን ይበልጥ ለማጠናከር ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በሃገራት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ የተከተለ ዲፕሎማሲን የሚያራምድ ፖሊሲ ነው። በሌላ መልኩልም ፖሊሲው የሃገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ከአህጉራዊና አለምአቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ያለው ተሳትፎ በማስተሳሰር ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ዓላማ አለው።

በዚሁ መሰረት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ያራምዳል፡-

1. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስከበርና ብሄራዊ ጥቅሞቿን ማስጠበቅ፣
2. ቀጠናዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትብብርና ትስስርን ማጠናከር፣
3. ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሰላምና ደህንነት እንዲሰፍን በጋራ መስራት፣
4. የገርን ሁለንተናዊ ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችሉትን ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን መሳብና ለኢትዮጵያ ወጪ ምርቶች ሰፊ የገበያ እድል መፍጠር፣
5. የቱሪዝም መስህቦችን በማስተዋወቅ ከመስኩ የሚገኘውን ጥቅም ማስፋት፣
6. የሀገሪቱን ታሪክ፣ ቱባ ባህሎችና ቅርሶች ማስተዋወቅ፣
7. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅም ማስከበር እና በውጭ የሚኖሩ የትውልደ-ኢትዮጵያውያን ጥቅም በህግ አግባብ የተጠበቀ እንዲሆንና በትውልድ-ሃገራቸው ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ እድሎችን ማመቻቸት፣
8. በአበይት ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔረዊ ጥቅምን ታሳቢ ማድረግ በትብብር እና በድርድር መስራትና
9. የድንበር-ተሻጋሪ የውኃ ሃብቶች በፍትሃዊ መልኩና በጋራ የመጠቀም ትብብር በማጠናከር የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

# 4.የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ስትራቴጂዎች

## 4.1 የሰላም ዲፕሎማሲ

ኢትዮጵያ በዓለም ዙሪያ ሰላም እንዲሠፍን የዓለም ሃገራት በመተባበር ለሰላም መስራት አለባቸው የሚል የፀና እምነት አላት። ሃገሪቱ የዓለም ማህበር አባል እና የተባበሩት መንግስታትና እንዲሁም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራችና የአፍሪካ ህብረት ዋና ጽ/ቤት መቀመጫም ናት። የውጭ ግንኙነት ፓሊሲው የሰላም ዲፕሎማሲን እንደ ዋነኛ ስትራቴጂ የሚያራምደው ሃገሪቱ ለሠላምና የጋራ ደህንነት ከምትሰጠው ልዩ ግምት የሚመነጭ በመሆኑ ነው።

### 4.1.1 የዓለም አቀፍ ሰላምና ደህንነት

የዓለማችንን ሰላም የሚያደፈርሱና ህዝቦችን ለስደት፣ እንግልትና ሞት የሚዳርጉ መንስኤዎች በርካታና ውስብስብ ናቸው። ኢትዮጵያ እነኚህን ዘርፈ-ብዙና አታካች ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከዓለም-አቀፍ ሠላም ወዳድ ኃይሎች ጋር ያላትን ግንኙነት አጠናክራ ትሰራለች። በአሁኑ ወቅት አክራሪነትና ሽብርተኝነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የሳይበር ጥቃት፣ የተደራጁ ድንበር-ዘለል ወንጀሎች፣ ህገ ወጥ የሰዎችና የመሳሪያ ዝውውር፣ ፅንፈኝነትና የንግድ ጦርነት እንዲሁም ሌሎች ወቅታዊ ችግሮች ባልተለመደ መልኩ ግጭቶችን እና አደጋዎች እያስከተሉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ቀጠናዊ ሰላም ካልሰፈነ ብቻዋን ሰላማዊ ሀገር ትሆናለች ተብሎ ስለማይታመን በዓለም-አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ክልላዊ ማዕቀፎች የተደነገጉ ስምምነቶችን በማክበርና በማስከበር ለአለም-አቀፍ ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ እያከናወነችው ያለውን ጥረት አጠናክራ ትቀጥልበታለች። ስለዚህም ግጭቶችን አለም-አቀፋዊ መርሆችንና በተከተለና በሰለማዊ መንገድ እንዲፈቱ ሀገሪቱ የምታደርገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

### 4.1.2 ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት

ኢትዮጵያ የተለያዩ ግጭቶች እንዳይከሰቱ አስቀድሞ መከላከልንና በሰላም ግንባታ ላይ ጠንካራ ስራ መስራትን ቅድሚያ የምትሰጠው ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶች አይነትና ውስብስብነት እየጨመረ በመምጣቱም በርካታ ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳት እየተከሰተ ይገኛል። እንደሚታወቀው ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ያልቻሉ ሃገራት ለከፍተኛ አገራዊ ቀውስና የብተና አደጋ ተጋላጭ ሆነዋል። ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱና እንዳይባባሱ ኢትዮጵያ

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት አባልነት፣ በአፍሪካ ህብረት ሰላምና ደህንነት ምክርቤት እና ኢ.ጋድ አማካይነት የሠላም አስከባሪነት ሚናዋን በመወጣት ላይ ትገኛለች። በዚህም ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ሰላምና መረጋጋት በአፍሪካ ቀንድ አከባቢ፣ በአፍሪካ እና በአለምአቀፍ ደረጃ እንዲሰፍን አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ሚናዋን እየተወጣች ትገኛለች። ይህንንም የምታደርገው የዓለም ሠላም ለሃገሪቱ ሠላምና ብልፅግና የሚኖረውን የማይተካ ቁልፍ ሚና በመገንዘብ ነው። በዚህም መሰረት ግጭቶችን ለመከላከልና ሲከሰቱም ለመፍታት በሰላም ግንባታ ዙሪያ የምታከናውናቸውን ስራዎች በይበልጥ አጠናክራ ተግባራዊ ታደርጋለች።

## 4.1.3 ሰላም ማስከበርና ስምሪት

ኢትዮጵያ የሀገራት የጋራ ደህንነትና ሠላም ሊረጋገጥ የሚችለው የዓለማችን አገራት ተባብረው ሲሰሩና የአለም-አቀፍ መርሆዎች መሰረት በማድረግ የጋራ እርምጃ ሲወስዱ ነው የሚል እምነት አላት። ሃገሪቱ እስካሁን በኮሪያ፣ በኮንጎ፣ በላይቤሪያ፣ በደቡብ ሱዳንና ሱዳን (አቢየ ግዛት) በሶማሊያ፣ በብሩንዲ፣ በሩዋንዳና በሌሎችም አገራት የተጣለባትን ዓለም አቀፋዊ አመኔታና ግዴታ በብቃት ለመወጣት የሰላም አስከባሪ ሃይል ስታሰማራ ቆይታለች። ኢትዮጵያ በሌሎች ሃገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የማትገባ ሲሆን ለሠላም ማስከበር ተልእኮ ጥሪ ሲቀርብላት የሰላም ማስከበር ሚናዋን በብቃትና በገለልተኝነት ተግባራዊ ታደርጋለች። በዚህ ረገድ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰላም ማስከበር ማዕቀፍ ሥር በርካታ የሰላም አስከባሪ አባላት በማዋጣት በተለይም የሴት ሰላም አስከባሪዎችን በመላክ በአለም-አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም ሃገር ናት። ከዚህ አኳያ በሰላም ማስከበር ስራ ላይ ሀገሪቱ የምታሰማራው የሰላም አስከባሪ ሃይል ተልእኮውን በብቃት የሚወጣ፣ በስነምግባሩና ቁርጠኝነቱ የተመሰገነ ሆኖ እንዲቀጥል አጠናክራ ትሠራለች።

## 4.2 የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ

### 4.2.1 ዓለምአቀፍ ንግድን ማስፋፋት

ኢትዮጵያ በዓለም-አቀፍ ንግድ ያላትን ሚና ማሳደግና ከዚሁ የምታገኘውን ጥቅም ማስጠበቅ ዋና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋ ተልእኮ ነው። ሃገሪቱ በዓለም አቀፍ የንግድ ትስስር ተጠቃሚ እንድትሆን ፖሊሲው የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ያራምዳል።

1. ከአፍሪካ፤ ከጎረቤት አገራት እና ሌሎች ታዳጊ ሃገራት ጋር ያለውን የንግድ ትስስር በማጠናከር የጋራ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
2. ህገ-ወጥ ድንበር-ዘለል ንግድን ለመቆጣጠር ከአጎራባች ሃገራት ጋር በቅርበት መስራት፣
3. በጎረቤት ሃገራት ያሉ የገበያ ፍላጎቶችን በማጥናት ለንግዱ ማህበረሰብ ማስተዋወቅ፣ የማበረታታትና የመደገፍ ስራዎችን ማጠናከር፣
4. እሴት የተጨመረባቸው ምርቶችን በውጭው ዓለም በተለያየ መልኩ በማስተዋወቅና ለገበያ በማቅረብ በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና ውስጥ የሀገሪቱን ድርሻ በአግባቡ መወጣትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ እንዲሁም የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን የሚደረገውን ጥረት በማጠናከር በዓለምአቀፍ የንግድ ትስስር ውስጥ መሳተፍ፣

### 4.2.2 ቴክኖሎጂ ሽግግርና የሳይንስ ዲፕሎማሲ

በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስክ ከአገራችን የቅድሚያ ትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የሚጣጣሙ ትብብሮችን መመስረት ተገቢ ይሆናል። በኢትዮጵያ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር የሚያካሂዱ ተቋማት በተለያዩ የአለም ክፍሎች ከሚገኙ ተቋማት ጋር በመተባበር የተሳለጠ ሣይንሳዊ ምርምር ለመስራት የሚችሉበትን ዕድል ማመቻቸት የዲፕሎማሲው አንዱ ትኩረት ይሆናል። ዲፕሎማሲው ለአገሪቱ ዕድገት ጠቃሚ የሆኑ የሳይንስ ምርምሮች እንዲጠናከሩና እንዲሸጋገሩ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። በዚህ ረገድ ውጤታማ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የሀገሪቱ የሴክተር መ/ቤቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል።

### 4.2.3 ኢንቨስትመንት

እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ ሃገራት የዉጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለኢኮኖሚ ዕድገት በተለይም ለውጭ ምንዛሪ ግኝት፤ ለቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም ለስራ ዕድል ፈጠራ የላቀ ሚና እንደሚኖረው ይታወቃል። የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ፉክክር ያለበት በመሆኑ በሃገር ውስጥ አመቺ ነባራዊ ሁኔታን መፍጠር የኢንቨስትመንት ፍሰቱን በማሳደግ ረገድ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል። ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የሚፈለገውን ኢንቨስትመንት ውጤታማ ለማድረግ የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን መስኮች በቅድሚያ በጥልቀት መረዳትና መለየት ያሻል። የዓለምአቀፉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችና ፍሰትን በአግባቡ ተረድቶ የኢንቨስትመንት ምንጭ የሆኑ ሀገሮችን ዝርዝር የኢኮኖሚ ፖሊሲና እነዚህ አባል የሆኑባቸውን የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች አሰራር በማወቅ ከሃገሪቱ ብሄራዊ ጥቅምና ፍላጎቶች ጋር አስተሳስሮ መሥራትን ይጠይቃል።

ስለዚህም ሥራ አጥነትን ሊቀርፍ በሚያስችል ተከታታይና ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ ኢንቨስትመንትን መሳብ የዲፕሎማሲው ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው። ይህን ዘላቂ ዕድገት የሚያረጋግጥ የሥራ ዕድልን ፈጠራ እውን ለማድረግ ልማትና ዕድገትን አጣምሮ ለማካሄድ ኢንቨስትመንትን በአግባቡ በመለየት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። ዲፕሎማሲው የሃገሪቱ ብሄራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የተለያዩ ኢንቨስትመንት ምንጮችን ማፈላለግ ተገቢ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በበለፀገው ዓለም የሚገኙ የኢንቨስትመንት ካፒታል ምንጮችና ክምችት የሚገኝባቸውን ሃገሮችና ተቋማት በመለየት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል። ይህ በተለይም በመንግስትና በግል ዘርፍ ትብብር ለሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ተፈላጊ የካፒታል ግብአትን ለማግኘት ያስችላል።

ዲፕሎማሲው ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ግንኙነት ማዕቀፍ እንዲጐለብትና ትስስር መፍጠር የሚያስችሉ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ተግባር ላይ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል። ለአብነት በቀጣናው በጋራ ሊለሙ የሚችሉ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ ያተኮረ የተጀመሩ የሰላምና የኢኮኖሚ ትስስር ፕሮጀክቶች የሚጠቀሱ ናቸው። ዲፕሎማሲው በቀጠናው የእሴት ፈጠራ ትስስር ሊያመጡ የሚችሉ ኢንቨስትመንቶች ላይ በማተኮር፤ በሃገሪቱ የግል ኢንቨስትመንትን ከማሳደግም አንፃር በተለይ የቴክኖሎጂ ሽግግርንና የስራ አመራር ክህሎትን ለማዳበር በሚያግዙ መስኮች ላይ ትኩረት በትጋት ይንቀሳቀሳል።

## 4.2.4 የልማትና የኢኮኖሚ ትብብሮች

ኢትዮጵያ አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባትና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ስትራቴጂ ቀርፃ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ከአየር ብክለት የነጻና በተለይም ታዳሽ የኀይል ምንጮችን ጥቅም ላይ ያዋለ ኢኮኖሚን ለመገንባት የተጀመረውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠልና ይህንን ስትራቴጂ ከሚደግፉ ሀገራት ጋር የተጀመረውን ግንኙነትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ፈጣንና ሁሉም በየደረጃው ፍትሃዊ በሆነ መንገድና የህግ የበላይነትን ባከበረ መልኩ ተጠቃሚ የሚሆንበትን የኢኮኖሚ ዕድገት በማረጋገጥ ዘላቂ ልማትን ለማምጣት የልማት ፋይናንስና የኢኮኖሚ ድጋፎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ፖሊሲው የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ይኖሩታል።

1. ከሃገራት ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ብሄራዊ ፍላጎቶችንና አቅምን ታሳቢ ያደረጉ አዳዲስ የፋይናንስ ምንጮችን ማፈላለግና መጠቀም፣
2. ከሃገራት ጋር የሚደረጉ ትብብሮች ሁለንተናዊ የፓለቲካና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በዘላቂነት ጥቅም የሚያስገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3. ለልማት አጋዥ የሆኑ የቴክኒክ ድጋፍና እርዳታ የሚሰጡ ሃገራት እና ተቋማትን መለየትና ዕድሎችን አሟጦ መጠቀም፣
4. በደቡብ - ደቡብ ትብብር ማዕቀፍ ውስጥ በመሆን የፋይናንስ ድጋፍ ምንጮችን መለየትና በዚህ ማዕቀፍ ሊገኙ የሚችሉ የሚገኙት ጥቅሞችን ማሳደግ፣
5. በአህጉር-አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የትብብር ማዕቀፎች አማካይነት የፋይናንስ ማግኛ እድሎችን ማስፋት፣
6. ከአለም-አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ የፋይናንስ እርዳታና ብድር የሃገሪቱን የኢኮኖሚ ፓሊሲ ነፃነት ባከበረ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

## 4.2.5 ቱሪዝም

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚገኙ ድንቅ የቱሪስት መዳረሻዎች ካላቸው አገራት አንዷ ብትሆንም ከዘርፉ የምታገኘው ጥቅም አነስተኛ ነው። ሀገሪቱ ያላትን የቱሪዝም ሃብት በአግባቡ በማሳደግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከዘርፉ ለመጠቀም የሚያስችላት ሰፊ ዕድሎች አሉ። ይህንን ዘርፍ ለማሳደግ የሚረዱ የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ የቱሪስት መስህቦች በሀገሪቱ ውስጥ ስለሚገኙ ህዝቦቿ ከዚህ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የውስጥ ሰላምና መረጋጋት ወሳኝ ነው። አንድ ቱሪስት ወደ ሌላ ሃገር ጉብኝት ከማድረጉ በፊት ከሚያያቸው መስፈርቶች መካከል የሚሄድበት አካባቢ ሰላም አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ስለዚህም መንግስትና ዜጎች ሰላምን ለማስጠበቅ መትጋት ይኖርባቸዋል።

የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው የቱሪዝም መስህቦችን ለማበልፀግ፣ ለማስተዋወቅና ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት ይሰራል።

1. የሀገሪቱን በጎ ገፅታ ለመገንባት ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት፣
2. "ምድረ ቀደምት" የኢትዮጵያ ብሄራዊ መለያ ሆኖ በዓለም ዙሪያ እንዲታወቅ ማድረግ፣
3. ሀገሪቱ እንደ የአፍሪካ ህብረትና የሌሎች ታላላቅ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች መቀመጫና በርካታ ኤምባሲዎች የሚገኙባት እንደመሆኗ እነዚህ የኮንፍረንስ ቱሪዝምን እድገት እንዲያግዙ ማበረታታት፣
4. ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩበት ሃገር ያሉ ቱሪስቶች ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ የሚያስችል መጠነ-ሠፊ እንቅስቃሴ ማድረግ፣
5. በአካባቢያው ካሉ አገራት ጋር ለጋራ ተጠቃሚነት በጥምረት በመስራት የቱሪስት ቅብብሎሽ ሂደት የሚያድግበትን ሁኔታ ማረጋገጥ።

## 4.2.6 የወደብ አገልግሎትና የማሪታይም ጉዳዮች

ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ያስመዘገበችውን ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ተከትሎ በከፍተኛ መጠን ያደገውን የገቢ እና ወጪ ንግድ በተቀላጠፈ መልኩ ለማስተናገድ በማሪታይም እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ አገራዊ አቅም ማሳደግ እና በዘርፉ በአለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ሀገሪቱ ካላት የህዝብ ብዛትና የኢኮኖሚ እድገት አንፃር የወደብ ባለቤት ከሆኑ ጎረቤት ሀገራት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

የባህር ትራንስፖርት ከሌሎች የትራንስፖርት ዘርፎች ጋር ሲነጻጸር በዋጋ ተመራጭና 90% የሚሆነው አጠቃላይ የዓለም የወጪና የገቢ ንግድ የሚጓጓዝበት በመሆኑ በዓለም የንግድና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ረገድ ጉልህ ድርሻ አለው። ኢትዮጵያም በአፍሪካ በርካታ ቁጥር ያላቸው መርከቦችን በማሰማራት የንግድ እንቅስቃሴ እያደረገች ሲሆን ይህንኑ ይበልጥ ማጠናከር ይስፈልጋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሀገሪቱ የአለምዓቀፉ የማሪታይምና የመርከብ አገልግሎት ውጤታማና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን አገራት የጋራ ሃላፊነት አለባቸው የሚል እምነት ታራምዳለች። በዚህም የመርከቦችና በባህር ላይ የሚደረገው ጉዞ ደህንነት የተጠበቀ ለማድረግ፣ በባህር በሚያደርጉ ጉዞ ላይ የአካባቢ ብክለት አደጋ ለመከላከል፣ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ እንዲሁም ዓለም አቀፉ የማሪታይም ኢንዱስትሪ የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲሰጥ በአህጉርና በአለምአቀፍ ደረጃ የወጡ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ የበኩሏን ግዴታ እየተወጣች ነው። ፖሊሲው በዚህ መስክ የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ይኖራሉ:-

1. የተሳለጠ የወደብ አገልግሎትና አማራጮችን ማግኘት የሚያስችሉ የትብብር ማዕቀፎችን መቀየስ፣
2. ወደብን በጋራ የማልማትና አስተማማኝና ደህንነቱ የተረጋገጠ የወደብ አገልግሎት ማረጋገጥና ሀገራትን የሚያገናኙ መሠረተ ልማቶችን ማጠናከር፣
3. የቀይባህርና የኤደን ባህረሰላጤ ከባቢዎች እንደ ጋራ ምህዳር ተወስደው ሀገሪቱ በአለምአቀፍ ህግ መሰረት በእነዚህ የመጠቀም መብቷን ማስጠበቅ፣
4. ከወደብ-አልባ ሃገራት ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ አለምአቀፍ ትብብርን ማጠናከር፣
5. ኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ ህጎችን በሚፈቅዱት መሠረት ለባህር በር የሚኖራትን የቀረቤታ ዕድሎችን የሚያሰፉ ሥራዎችን በትጋት ማካሄድ፣
6. ሀገሪቱ የምታሰለጥናቸው ባህርተኞች በአለምአቀፍ የመርከብ ድርጅቶች ተቀጥረው እንዲሰሩ የሚያስችሉ እድሎችን ማመቻቸት፣
7. የሀገሪቱን የማሪታይም ጥቅምና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያሰችል ሁለንተናዊ አቅም መገንባትና ከጎረቤት ሀገራት ጋር በቅርበትና በትብብር መስራት፣

## 4.3 ዜጋ-ተኮር ዲፕሎማሲ

የዓለም ሃገራት በውጭ ሃገር በሚገኙ ዜጐቻቸው አማካይነት በርካታ ጠቃሚ ተግባራትን ያከናውናሉ። በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ የመሳተፍ ከፍተኛ ሚና አላቸው። የዜጋ-ተኮር ዲፕሎማሲ እነዚህን የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት አውታር አካል አድርጐ ይመለከታል። ይህም ዜጎችና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በተናጠልና በሽርክና በኢንቨስትመንትና ንግድ እንዲሁም በቱሪዝም መስኮች በመሰማራት፤ በቴክኖሎጂና ሳይንስ እንዲሁም የክህሎትና ዕውቀት ሽግግር አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን ተግባራዊ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝት መጠን እንዲያድግና በኢንቨስትመንት የሚኖራቸው ድርሻ እንዲያድግ እንዲሁም ሃብታቸውን ወደ ኢትዮጵያ በህጋዊ መንገድ እንዲልኩ ማትጋት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በሚኖሩበት ሃገር ላይ የልማት ፋይናንስ በማፈላለግና በገጽታ ግንባታና ማስተዋወቅ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው።

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ-ኢትዮጵያውን ከአገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ለማጠናከር ሃገራቸውን የተመለከተ ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ በሀገሪቱ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥራ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ያስፈልጋል።

የውጭ ግንኙነት ፓሊሲው ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት ሃገር እንደ አግባቡ ደህንነታቸው እና መብታቸው እንዲጠበቅና እንዲከበር ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። ዜጐች ወደ ሌላ ሃገር ለሥራ ከመሄዳቸው በፊት ህጋዊ የውጭ ሃገር የስራ ስምሪት ስምምነቶችን በማድረግ ለደህንነታቸው ዋስትና እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ ነው። ወደ ውጭ ከሄዱም በኃላ መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር በሚያስችል መልኩ በመስራት በአገራቸው ጉዳይ ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚያስችላቸው አሰራር ይዘረጋል።

በሌላ መልኩ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ስርጭት እንደ የሃገሩ የሚለያይ ስለሆነ እንደ ሁኔታ፤ የተሰማሩበት የስራና ሙያ መስክ ፤ ጾታ፤ ዕድሜ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት መረጃዎችን በዘመናዊ አግባብ ማደራጀት ለአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና በሚያመች መልኩ

መብትና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሚያስችል መልኩ የተቀናጀ የመረጃ ስርዓት ተጠናቅሮ ሥራ ላይ ይውላል።

በዚህ ረገድ ፖሊሲው የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ይኖሩታል።።

1. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን መብት ማስከበር፣
2. በውጭ የሚኖሩ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ጥቅም እንዲከበር መደራደር፣
3. በሀገሪቱ ህጎችና ፓሊሲዎች አግባብ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳች ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ማረጋገጥ፣
4. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውን ሃብቶቻቸውን በህጋዊ መንገድ መላክ እንዲችሉና እንዲያስቀምጡ ልዩ ማበረታቻ መስጠት፣
5. በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ትውልደ-ኢትዮጵያን በኢትዮጵያ ውስት የተቀላጠፈ አገልግሎት ማቅረብ፣

## 4.4 ፐብሊክ ዲፕሎማሲ

በዓለምዓቀፍ ግንኙነት መስክ ከተለመደው የመንግስት-ለመንግስት ግንኙነት ባሻገር በውጭ ግንኙነት ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚችሉ በርካታ መንግስታዊ-ያልሆኑ ተዋናዮች እየተበራከቱ መምጣታቸው ተስተውሏል። እነዚህም የራሳቸው በርካታ ተከታዮች ያሏቸውና ህብረተሰብን በተለያዩ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች አሰልፈው እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ናቸው። ከመንግስታት ጋር በሚያደርጉት ግንኙነትም የመንግስታቱን የፖሊሲ አቅጣጫ ከመቅረጽ፤ ከመደገፍ አልያም በተቃውሞ በመቆም ፖሊሲ የማስቀየር አቅምና ተፅዕኖ የማሳደር ኃይል ፈጥረዋል።

በሌላ መልኩ እጅግ ፈጣንና በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ እየተተስፋፋ መምጣት የመንግስትን መረጃ የመቆጣጠር አቅም በእጅጉ በመለወጥ የመረጃ ሰጪውንም ሆነ የተቀባዩን አድማስና ተሳትፎ እያሳደገ ይገኛል። ይህም የመንግስታቱን የመረጃ ፍሰትና ስርዓት የመቆጣጠር አቅም በመቀነስ ሌሎች ተሳታፊዎች በመረጡት መንገድ ሃሳባቸውና ፍላጎቶቻቸውን ለማቅረብ የሚችሉበትን ዕድል በእጅጉ አስፍቶታል። ስለሆነም ሀገራት ባለንበት ነባራዊ ዓለም ዲፕሎማሲን ለማካሄድ ከመንግስታት ውጪ ያሉት ተዋንያን በዓለምአቀፍ ግንኙነት መስክ ያላቸውን ተሳትፎ

ታሳቢ በማድረግ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለማስፈፀምና ለማሳለጥ ፐብሊክ ዲፕሎማሲን ሲጠቀሙ ይታያል።

ኢትዮጵያም ይህንን ከነባራዊው ዓለም ተጨባጭ ለውጦች ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ መጠቀም ይገባታል። ከዚህ አኳያ ሀገሪቱ ያሏትን ጠንካራ እሴቶች መሰረት በማድረግ በመረጃ ሥርጭት ሥራዎች፤ በገጽታ ግንባታና በህዝብ-ለህዝብ ግንኙነት ማጠናከሪያ መንገዶች የተደገፈ ዲፕሎማሲ ታራምዳለች። በአፈፃፀም ረገድም የፐብሊክ ዲፕሎማሲ የትግበራ አቅጣጫዎች ሦስት ዓበይት ክፍሎች ለይቶ እንደአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። እነዚህም በመደበኛውም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ የሚደረጉ ግንኙነቶች፤ የተለያዩ ሁነቶችና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የሚከናወኑ ተግባራት፣ በረጅም ጊዜ ሂደት ጠንካራ የሕዝብ-ለህዝብ ግንኙነቶችንና የሚያጠናክሩ በፓርላሜንታዊ፣ በትምህርት ተቋማት እንዲሁም በከተሞች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች ናቸው።

## 4.4.1 ሚዲያ

ኢትዮጵያን አስመልክቶ በውጭ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ የሚዲያ ግንኙነት ስትራቴጂ መንደፍ ይስፈልጋል። በሃገር ውስጥም ህዝቡ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አፈፃፀም ዙሪያ ወቅታዊና ፈጣን መረጃ የሚያገኝበትንና ተሳትፎውን የሚያሰፋበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም ዲጂታል ዲፕሎማሲንና የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው የሀገሪቱን እሴቶች ለተደራሾች ማጋራት እና ደጋፊዎችን ለማበራከት የተግባር አቅጣጫ ማመላከቻ ይሆናል።

## 4.4.2 ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶች

ኢትዮጵያ ያሏትን እጅግ የካበተ የባህልና የታሪክ እሴቶችን ማዕከል አድርገው በተቀረፁ ጭብጦች ዙሪያ የገጽታ ግንባታ ፕሮግራሞችና ሁነቶችን በማዘጋጀት ለዓለም ህብረተሰብ የማስተዋወቅ ሥራ ይከናወናል። የሙዚቃ፣ ስፖርት፣ ስነ-ስዕል፣ ስነ-ጥበብ ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን በመጠቀም የህዝብ-ለህዝብ ግንኙነት ማጠናከሪያ ፕሮግራሞችና ዝግጅቶች በማካሄድና ማከናወን በውጪው ማህበረ-ሰብ ዘንድ የሃገር ገጽታ የመገንባትና የማስተዋወቅ ሥራን ማጠናከር ያስፈልጋል።

### 4.4.3 ህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችና ጉድኝቶች

የህዝብ-ለህዝብ ግንኙነቶች በዋናነት በሀገሪቱ ተቋማት እና በሌሎች ሃገራት ተቋማት መካከል ዘለቄታዊ ግንኙነቶች መመስረት ላይ ያተኩራል። የረጅም ጊዜ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት አካሄድ በተለይ በልሂቃንና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል በሚደረግ ትስስር፣ በፓርላማዎች መካከል በሚደረጉ ጉድኝቶች፣ በከተሞችና በጥናትና ምርምር ተቋማት እንዲሁም በታዋቂ ግለሰቦች መካከል የሚደረጉ መስተጋብሮችን ታሳቢ አድርጎ ይከናወናል። ይህንን ተግባራዊ በማድረግም ለብዙሃን ተደራሽ የሆነና ወደጆችን ማበራከት የሚያስችል የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል።

# 5.ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች

## 5.1 የአየር ንብረት ለውጥ

ኢትዮጵያና በማደግ ላይ የሚገኙ አብዛኞቹ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ እዚህ ግባ የሚባል አስተዋጽኦ ባይኖራቸውም የዚህ ተግዳሮት ዋና ሰለባ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ስለሆነም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም በአለምአቀፍ ደረጃ የተጀመሩትን የጋራ ጥረቶች ከአፍሪካ ሃገራት ጋር በመሆን የጋራ አቋም በመያዝ መታገል ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳቶችን ተገንዝበው በውጭ ፖሊሲያቸው ለመፍትሄው የጋራ አቋም ከሚያራምዱ አገራት ጋር ኢትዮጵያ በትብብር በመሥራት የበኩሏ አስተዋፅኦ ለማበርከት ትሠራለች፡፡ በዚህ ረገድ በአንድ በኩል በሃገሪቱ ውስጥ የሚከናኑ ስራዎችና ውጤት የተገኘባቸውን ተሞክሮዎች አለምአቀፍ እውቅናና ድጋፍ እንዲያገኙ መስራት በሌላ በኩል ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚደረጉ የጋራ ጥረቶች አካል በመሆን በግንባር ቀደምትነት መሳተፍ ተገቢ ነው፡፡

## 5.2 ፍልሰትና ስደተኝነት

ኢትዮጵያ ስደተኞችን ተቀብሎ የማስተናገድ እና ከጥቃት የመከላከል ለዘመናት የዘለቀ የምትከራበት ታሪክ አላት፡፡ አሁንም በአብዛኛው በተለያዩ ምክንያቶች ከጐረቤትና ሌሎች ሃገራትየመጡ ስደተኞችን ስታስተናግድ ቆይታለች፡፡ ስደትና ፍልሰት ዓለምአቀፍ ችግር ሲሆን ኢትዮጵያም የነዚህ ማህበራዊ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው አካል ናት፡፡ ሀገሪቱ ውስን ሃብት ያላት ቢሆንም በተለያየ ምክንያት ተሰደው የሚመጡ የጎረቤት ሃገር ህዝቦች በማስጠለል ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታለች፡፡

በሌላ መልኩ ሀገሪቱ የስደተኞች ምንጭና ወደሌላ ሃገር ለሚሄዱ የሌሎች ሃገራት ስደተኞችም እንደ መሸጋገሪያ ሆና የምታገለግል ናት፡፡ በዚህ ረገድ ፓሊሰው የሚከተሉትን ስትራቴጂዎች ይኖሩታል፡፡

1. ስደትና ፍልሰትን ለማስቆም የችግሩ ምንጭ የሆኑ እንደ ግጭት፤ የአየር ንብረት ለውጥ፤ ረሃብ፤ ስራ-አጥነት፣ የመልካም አስተዳደር እጥረት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ለማስወገድ ከሌሎች አጋሮች እና ተዋናዮች ጋር በትብብር መስራት፣
2. ስደትና ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተፈረሙ አህጉራዊ እና ዓለምአቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ማድረግ፣

3. በቀጣናውና በአህጉሩ ግጭቶች እንዳይከሰቱ፤ ከተከሰቱም ሰላማዊ መፍትሄ አግኝተው በግጭት ምክንያት የተሰደዱ ሁሉ ወደ ሀገራቸው መመለስ እንዲችሉ በትብብር መስራት፣
4. ፍልሰትን እና ስደትን በተመለከተ በባለብዙ ወገን መድረኮች ላይ በንቃት በመሳተፍ ችግሮች የጋራ መፍትሄ እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ፣
5. በተለያዩ ሀገራት በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በፍቃደኝነት ወደ አገራቸው እንዲመለሱ እና እንዲቋቋሙ ከሌሎች ሃገራት ጋር በትብብር መስራት፣

## 5.3 ዘላቂ ልማት

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት ተስማምተው ባፀደቁት አጀንዳ 2030 የተካተቱትን 17 የዘላቂ ልማት ግቦች በሀገሪቱ ውስጥ እውን ለማድረግ፤ በዓለምአቀፍ፤ በአህጉርና በክፍለ-አህጉር ደረጃ ከሚገኙ ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በትብብር መስራት እንደሚያስፈልግና ለዚህም ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ፖሊሲው ትኩረት ይሰጣል። በዚህም ረገድ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተነደፈውን የዘላቂ ልማት ግቦች ለማስፈፀም ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ኢትዮጵያ ከአጋር ሀገራት ጋር በትብብር መስራት እንደሚያስፈልግ አጥብቃ ታምናለች።

## 5.4 የሳይበር ቴክኖሎጂ

የሳይበር ቴክኖሎጂ ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በአለምአቀፍ ደረጃ ለሚታየው የማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብርና ለውጥ ከፍተኛውን ሚና እየተጫወተ የሚገኝ ሲሆን አገራት የዚህ ቴክኖሎጂ ጥገኛ የመሆናቸው ሂደትም በየጊዜው እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል። የሳይበር ቴክኖሎጂ በአለማችን አዳዲስ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ወታደራዊና የዲፕሎማሲ መስተጋብሮች እንዲፈጠሩ አዳዲስ እድሎችና ስጋቶችን ይዞ በመቅረብ ዘርፈ-ብዙ ለውጥ አስከትሏል። የሳይበር ቴክኖሎጂ በአጠቃላይ ከግለሰብ መረጃ ጀምሮ እስከ ሃገር ድረስ ቁልፍ ልዩ ልዩ የሲቪልና ወታደራዊ ሃብቶች የሚከማቹበት አውድ ሆኗል።ሀገራትም የዚህ ቴክኖሎጂ ጥገኛ የመሆናቸው ጉዳይም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና ከዛ ውጭ መኖር አማራጭ የሌለው ሂደት እየሆነ መጥቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ቴክኖሎጂው ይዞት የመጣው መልካም አጋጣሚ እንደተጠበቀ ሆኖ በመስኩ ሃገር-በቀል አቅም በአግባቡ ካልተፈጠረና በአጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ስርአት እና ህግ ካልተበጀለት ስጋትና አደጋም ማስከተል እንደሚችል መገንዘብ ይገባል። በተለይም በአሁኑ ወቅት የኢንተርኔት ተደራሽነት በአለም አቀፍ ደረጃ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሳይበር ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚፈፀሙ ወንጀሎች ድንበር ሳያግዳቸው በየትኛውም ቦታና ሰዓት የመከሰታቸውን እድል ሰፊ አድርጎታል። ይህም በሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻከር ተፅእኖ እየፈጠረ ይገኛል።

የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው የሳይበር ቴክኖሎጂ በተመለከተ ከሀገራት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በተመለከተ የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ይከተላል።

1. የሳይበር ምህዳር የማይታይና የማይዳሰስ ድንበር-የለሽ የኮምፒዩተር ስርዓትና ትስስር በመሆኑ ሀገሪቱ በዘርፉ የሚገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ እንድትችል በአለም-አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የትብብር ማዕቀፎች ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
2. ቴክኖሎጂው የተራቀቀ የግንኙነት መርበብን በመጠቀም የሚከናወኑ ህገ-ወጥ ድርጊቶች በአብዛኛው የፖለቲካ አጀንዳ ተልእኮ ያላቸውና በብሄራዊ ጥቅሞች ላይ የሚያነጣጥሩ በመሆናቸው እነዚህንና መሰል ጥቃቶችን በብቃት ለመመከት በመስኩ ልምድ ካላቸው አገራት ጋር በትብብር መስራት፣

## 5.5 የጠፈር ሳይንስ ጉዳይ

ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ራሷን የቻለች ሃገር ለመሆን የምታደርገውን የጥናት፣ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ እና የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ በተለይም በኤሌክትሮኒክ ኮሚኒኬሽን ረገድ በሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች የህዋው ሳይንስ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ለዚህም ሀገሪቱ በመስኩ ከሰለጠኑ አገራት ጋር በጋራ በመሥራት የራሷንና የዓለም-አቀፍ ደህንነት ለማስጠበቅ በትብብር ትሳተፋለች። የጠፈር ሳይንስ ለሀገር ልማት የሚያኖረውን አስተዋፅኦ ታሳቢ በማድረግ በመስኩ የዳበረ ልምድና ተሞክሮ ካላቸው አገራት ጋር ግንኙነት ማጠናከርና ተጨባጭ የአቅም ግንባታ ማካሄድና የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፎች ማሰባሰብ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በአህጉርና በአለምአቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ትብበሮች ተሳትፎዋን አጠናክራ ትቀጥላለች።

## 5.5 ተፈጥሮ ሀብትና ኢነርጂ

በአለማችን ላይ የተስተዋሉ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቶች በዋነኛነት መሰረት የሚያደርጉት የተፈጥሮ ሃብትን በመጠቀም መልማት ሲሆን ዛሬም በኢንዱስትሪ የበለፀገ አገራት የተፈጥሮ ሃብትን በስፋት ይጠቀማሉ። የተፈጥሮ ሃብት ውሱንነት የአገራት የልማትና ትብብር ምንጭ ወይም የግጭትና ብጥብጥ መንስዔ ሊሆን እንደሚችል የዓለምአቀፍ ነባራዊ ሁኔታ ያመላክታል።

ኢትዮጵያም ያላትን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ በመለየት ለዘላቂ ልማትና ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባት ፖሊሲው አጽንኦት ይሰጣል። ድንበር-ተሻጋሪ የተፈጥሮ ሃብቶች የትብብር መንስዔ መሆን ይችሉ ዘንድ ከጐረቤት ሀገራት ጋር በትብብር በማልማት በሂደት ላይ ለሚገኘው ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር አጋዥ መሳሪያ አድርጎ መጠቀም ይገባል። በዚህም ሀገሪቱ የመሪነት ሚና በመጫወት የጋራ ሃብቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለጋራ ተጠቃሚነት እንዲውሉ ትሰራለች።

ኢትዮጵያ ሰፊ የሃይል ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ የተፈጥሮ ሃብቶች ባለቤት ከመሆኗም በላይ እያደገ ከመጣው ኢኮኖሚዋ ጋር በተያያዘ የኢነርጂ ፍላጐቷ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨምሯል። ታዳሽ የሃይል ምንጭ ልማት የሃገር ውስጥ የሃይል ፍላጐትን ከማሟላት በተጨማሪ ለቀጠናው የኢኮኖሚ ትስስር ማሳለጥ የሚኖረው ድርሻ ታሳቢ ሆኖ እየተሰራበት ነው። ይህንኑ በቀጣይ አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል። በተጨማሪም ከታዳሽ የሃይል ምንጭ ሃብቶች ጎን ለጎን የኑክሊየር ሃይልን ለሰላማዊ ልማት የማዋልና እንደ ሃይል ምንጭ መጠቀምን ታሳቢ ያደረገ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባል።

## 5.6 ሰብአዊ ጉዳዮች

ኢትዮጵያ በተለያዩ ምክንያቶች ለሚከሰቱ የሰብዓዊ ቀውሶችን ከሌሎች ሃገራትና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር አቅምን ያገናዘበ ድጋፍ የምታደርግ ሲሆን የሰብአዊ ርዳታና ድጋፍ የሚሹ ጉዳዮች በአጐራባች ሀገራት እና ሌሎች አፍሪካ ሀገራት ላይ ሲከሰቱ፣ ሀገሪቱ በፈረመቻቸው አህጉራዊና አለም-አቀፍ ህግጋት መሰረት ሰብዓዊ እርዳታ በተቀናጀና በተቀላጠፈ መልኩ ለተጐዱ ወገኖች እንዲደርስ ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር በትብብር ትሰራለች።

ኢትዮጵያ በአህጉርና በአለም አቀፍ ደረጃ የፈረመቻቸው የሰብዓዊ እና የህዝብ መብቶች ስምምነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ በትብብር ትሰራለች። የሰብአዊና የህዝብ ዴሞክራሲያው መብቶች የሀገራት ሉኣላዊነትን ባከበረና የሰው-ልጆች ነፃነትና መብቶች እንዲረጋገጡ ድጋፍ ታደርጋለች።

# 6.ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም-አቀፋዊ ግንኙነቶች

## 6.1 ጐረቤት አገሮች

የአፍሪካ ቀንድ በቅርብ ርቀት የሚገኙ የታሪክ፣ የባህል፤ የቋንቋ፣ የመልክአምድር እና የህዝቦች ትስስርን ያካተቱና ኩታገጠም የሆኑ ሃገራትን ያካትታል። እነዚህ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋር መፃኢ እድላቸውና እጣ-ፈንታቸው የተሳሰረ ነው። ለዘመናት በዘለቀው የሀገሪቱ ታሪክ ኢትዮጵያ ከጐረቤቶቿ ጋር ለዘመናት የዘለቀ ግንኙነት አላት።

የአፍሪካ ቀንድ ሃገራት የሚመሳሰሉበት እና የሚለያዩበት የህዝብና የመልክአ-ምድር ሁኔታ እንዳለ ሁሉ በኢኮኖሚያዊ መስኮችም ተመሳሳይ ትስስር አላቸው። ኢኮኖሚያቸው በአብዛኛው በግብርና እና ማዕድን ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም በላይ ምርታማነቱ እምብዛም ነው። ሃገራቱ ሊለማ የሚችል ሰፊ እምቅ የሀብት አቅም ቢኖራቸውም ህዝቦቻቸው አሁንም በድህነት እየማቀቁ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀንድ ሃገራት ጋር ያላት ግንኙነት በጥብቅ የተሳሰረ እንደሆነ በመገንዘብ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ለጐረቤት ሀገሮች ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

### 6.1.1 የፖለቲካ ጉዳዮችና ዓለም አቀፍ መድረኮች

ሀገሪቱ ከጐረቤት አገሮች ጋር የሚኖራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን ፖሊሰው ያሰምርበታል። ለዚህም ከጐረቤት አገሮች ጋር መደበኛና ወቅትን የጠበቀ የፖለቲካ ምክክርና የጋራ የሚኒስትሮች ጉባኤዎችን በማካሄድ በቀጠናው፤ በአህጉርና በባለብዙ ወገን መድረኮች በትብብር ሊሰሩባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት የጋራ አቋም ታራምዳለች። ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች በምታራምዳቸው አቋሞች ሁሉ የጐረቤት አገራትን ጉዳይ ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ መሆኑን ታምናለች። በዚህ ረገድ በቀጠናው እና በጐረቤት አገራት የሚኖሩ ለውጦችንና ክስተቶችን ልዩ ትኩረት ሰጥታ በቅርበት ትከታተላለች።

በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ በሚገኙ ጐረቤት ሀገሮች መካከል በተለይ በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው መልካም የሚባል ዘርፈ-ብዙ ግንኙነት እንዳለ ይታወቃል። በሶሺዮ-ኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካው መስኮች ያለው ትብብርም በመልካም ጅማሮዎችና ሂደቶች ይገለፃል። እነዚህን በከፍተኛ ደረጃ አጠናክሮ ለመራመድ በመልካም ጉርብትና በገለልተኛነት እና የጐረቤት ሀገሮችን ሉዓላዊነት

በሚያከብሩ መርሆዎች መመራት ያስፈልጋል። በተጨማሪም የጋራ ጥቅምን በሚያረጋግጡና ቀጣይነትን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን ማከናወን አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ረገድ ያሉትን መልካም ግንኙነቶች የሚመጥኑ የጋራ ትብብሮችን በማጠናከር የችግሮችን ምንጭ በውይይት፣ በድርድር እና በመደጋገፍ መንፈስ መፍታት እንዲሁም ለጋራ እድገት የመሥራት ጉዳይ በትጋት ትቀጥልበታለች።

## 6.1.2 አካባቢ ደህንነትና ሰላምን ማረጋገጥ

የአፍሪካ ቀንድ ለረጅም ጊዜ በጦርነት፤ በረሃብ፤ በስደተኞች ፍልሰትና በመንግስታዊ መዋቅሮች መዳከም የሚታወቅ አከባቢ ነው። ባለፉት ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ የተገኘውን አንፃራዊ ሰላም አስተማማኝና ዘላቂ ለማድረግ በተወሰደው እርምጃ አበራታች ውጤት ተገኝቷል። ይህ እርምጃ የአፍሪካ ሕብረትን በመርህ ላይ የተመሰረቱ አሰራሮች ተግባራዊ በማድረግ ይሰራል።

የቀጠናውን ሰላምና ደህንነት በማስከበረ ረገድ የበይነ-መንግሥታት ባለሥልጣን (IGAD) አስተዋጽኦ የጎላ ነበር። በተለይ ሀገሪቱ ለቀጠናው ሰላምና ደህንነት በባለሥልጣኑ ጥላ ሥር የምትጫወተውን ሚና አጠናክራ የሚትቀጥል ከመሆኑም ባሻገር የተቋሙ የእንቅስቃሴ አድማሱ በማስፋት ይበልጥ እንዲጎለብት ለማድረግ ከአባል ሀገራቱ ጋር ተባብራ የበኩላን አስተዋጽኦ ታደርጋለች።

በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት በዘላቂነት እያደገ እንዲሄድና መሰረት እንዲይዝ ማድረግ ለእድገትና ልማት መጠናከር ወሳኝ ሚና አለው። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ክስተቶች በጐረቤት ሀገሮች ላይ ተመሳሳይ እንደምታ የሚኖራቸውን ያህል በእነርሱም በኩል ያሉት በኢትዮጵያ ላይም ተፅዕኖ ያሳድራሉ። በመሆኑም ሃገራቱ የአካባቢ ደህንነትና ሰላም ለማረጋገጥ በትብብር የመሥራት ጉዳይ ቁልፍ ነው።

## 6.1.3 ኢኮኖሚያዊ ትስስር

አሁን ባለንበት የአለም-አቀፍ ሁኔታ ኢትዮጵያ ዘላቂና የተሳካ የኢኮኖሚ እድገት የሚኖራት ከጐረቤት ሃገራት ጠንካራና የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስሮች እና ግንኙነቶች ተጠናክረው ሲቀጥሉ ነው ብላ ኢትዮጵያ ታምናለች። ከዚህ አኳያ

ከጐረቤት ሃገራት ጋር የጋራ ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ዙሪያ በትኩረት የመሥራትን አስፈላጊነት ፖሊሲው ያበረታታል። በተለይም ቀጠናው በመሰረተ-ልማት አውታሮች እንዲገናኝ፣ ነፃና ህጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ እንዲሁም ህገ-ወጥ የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል የሚያስችል ሥራ በጋራ መስራት የፖሊሰው የትኩረት አቅጣጫ ነው።

የጐረቤት ሃገራት ለኢትዮጵያ የወጪ ምርቶች ገበያ ከመሆናቸው በተጨማሪ እያደገ ያለው ኢኮኖሚዋም የጋራ የገበያ እድሎችን ሊፈጥር የሚችል መሆኑን ፖሊሲው ታሳቢ ያደርጋል። ኢትዮጵያ በጐረቤት ሀገሮች ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን የማምረት ዕድል አላት። ይህንን ዕድል ለመጠቀም የሚያስችሉ አቅሟን በማጐልበት ሊኖር የሚችለውን የገበያ እድሎችን በአግባቡ በመለየት ከዚህም ለመጠቀም በትኩረት መስራት ያስፈልጋል። ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትሪ በምታደርገው ሽግግር ጐረቤቶቿ በተሻለ ዋጋና ጥራት ሊያገኟቸው የሚችሉ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በማስተዋወቅ ተወዳዳሪ ለመሆን እንዲችሉ መስራት እንደሚገባ የውጭ ግንኙነት ፖሊሰው አጽንኦት ይሰጣል።

ኢትዮጵያ ከጐረቤት ሃገራት ጋር በተለየ ሊያስተሳስሩ እና በጋራ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ የኢንቨስትመንት መስኮችን በመለየት በትብብር መስራት ያስፈልጋታል። ሀገሪቱ ከጐረቤት አገሮች ጋር በጋራ ወይንም በተናጠል በምታደርገው ስምምነት መሰረት ዙሪያ-መለስ ኢንቨስትመንትን ታበረታታለች። በዚህም ሀገሪቱና ጐረቤቶቿ የተለያዩ የተፈጥሮ፤ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦች ያሉዋቸው በመሆናቸው በቱሪዝም መስክ በትብብር በመስራት በቀጣናው ያሉ የቱሪዝም ተቋማት ተቀናጅተው እንዲሠሩ የሚያስችሉ የጋራ ጥረቶች ይደረጋሉ።

በቀጠናው ያሉ አገሮች በታሪክ፤ በባህልና ማህበራዊ ኑሮ የተሳሰሩ በመሆናቸው ይህንን በጐ አጋጣሚ ለጋራ ጥቅም ለማዋል የሚያስችል የኢኮኖሚ ትስስር እውን እንዲሆን በትብብር ለመሥራት ጥረት ይደረጋል። ለዚህም ሀገሪቱ ከጐረቤት አገራት ጋር የሚያስተሳስሯት የተጀመሩ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ተግባራዊነት አጠናክራ ትቀጥላለች። የቀጠናውን የኢኮኖሚ ትስስር ከሚያፋጥኑ ጉዳዮች መካከል የተናበቡና የተቀናጁ ወይም የተጣጣሙ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን መቅረጽ አንዱ ነው። በመሆኑም አገራችን በቀጠናው የተናበበ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲኖር በክልላዊና በክፍለ አህጉራዊ ተቋማት በኩል ከምታደርገው ጥረት በተጨማሪ ከጐረቤት አገሮች ጋር የምክክር የጋራ ኮሚሽን በማቋቋም እና ይህንኑ በማጠናከር የቀጠናው የኢኮኖሚ ትስስር እንዲፋጠን ትሰራለች።

የጋራ የድንበር ልማትም ትኩረት ተሰጥቶት የሚተገበር ይሆናል። ኢትዮጵያ በቀጠናውና በአህጉር ደረጃ የሚገኙ እና የኢኮኖሚ ትስስር የሚያስተባብሩ በይነ-መንግስታዊ ተቋማት በተለይ የበይነ-መንግስታት የልማት ባለሥልጣን(IGAD) ተቋማዊ አቅሙ እንዲጠናከር፣ የማስተባበርና የማስፈፀም አቅም እንዲጎለብት ድጋፏን በማጠናከር በዚህ ረገድ ከአባል ሀገራት ጋር ትኩረት ሰጥታ በትብብር ትሰራለች።

## 6.1.4 የህዝብ ለህዝብ ትስስርና ግንኙነት

ከጐረቤት ሀገሮች ጋር ኢትዮጵያ የምትጋራቸው በርካታ ተመሣሣይ ባህልና እሴቶች ቢኖራትም እነዚህን በማሳደግ ግንኙነቶችን ወደ ላቀ ምዕራፍ በማሸጋገር ረገድ የተሰራ ስራ ውሱን ነው። ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ከጎረቤቶቿ ጋር የፈጠረችው ግንኙነት በአሁኑ ወቅት የተሻለ ገጽታ እንዲኖር ያስቻለ ቢሆንም ይህንኑ አጠናክሮ ለማስቀጠል ከጐረቤት ሀገሮች ጋር የሚደረግ የህዝብ ለህዝብ ትስስር እና የገጽታ ግንባታ ስራ ማካሄድ የውጭ ግንኙነት ፖሊሰው ትኩረት ነው። በዚህ ረገድ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ መሳሪያዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋልና የሀገሪቱ ሚሲዮኖች ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ  ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ እና ጎረቤት ሃገራት ህዝቦች መካከል ያለው የዝውውር እንቅስቃሴ ከፍተኛ ነው። በድንበር አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች በባህል፣ ሃይማኖትና ታሪክ የተሳሰሩና ለሃገራቱ ግንኙነቶቹ እንደ ድልድይ ያገለግላሉ። በጎረቤት አገራት የሚኖሩ ኢትዮጲያውያን መብታቸው፣ ክብራቸው እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ በኢትዮጵያ የሚኖሩ የጎረቤት አገራት ዜጎች በተመሳሳይ መብትና ጥቃማቸው እንዲጠበቅ የሚረዱ እና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ ይበልጥ የሚያጠናክሩ ሥራዎች ላይ  መሣተፍን ፖሊሰው ትኩረት ይሰጣል።

## 6.1.5 የወደብ አገልግሎት

ኢትዮጵያ በህዝብ ብዛት በዓለም ቀዳሚ ወደብ አልባ ሀገር ናት። ለወደቦችም በቅርብ ርቀት የምትገኝ ሲሆን ከእነዚህ ጋርም በመሰረተ ልማት ትገናኛለች። የተቀላጠፈና ፈጣን የወደብ አገልግሎትን ማግኘት ለኢትዮጵያ ወሳኝ በመሆኑ የወደብ ጉዳይ የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ከባለወደብ ሃገራት ጋር ዘላቂ የወደብ አገልግሎትና የባህር በር መዳረሻ የማግኘት መብቷን በሚያረጋግጡ ዓለም አቀፍና ቀጠናዊ ትብብሮች ዙሪያ የመሥራትን ጉዳይ አጥብቃ

ትቀጥላለች። በዚህም ወደብን በጋራ ለማልማትና አገልግሎትን የሚያሳልጡ ስራዎች ተግባራዊ ታደርጋለች። ይህንን እውን ለማድረግ፡-

1. ሀገሪቱ አዋጭ በሆነ መንገድ የምትገለገልባቸው አማራጭ የወደብ አጠቃቀም እድሎችን ታሳቢ በማድረግ አስተማማኝ አገልግሎት የሚሰጡትን በመለየት ከጎረቤት አገሮች ጋር ወደብ እና የትራንዚት ኮሪደሮችን በጋራ ማልማት፣
2. የወደብ አገልግሎቶች አስተማማኝ፤ ደህንነታቸው የተጠበቀና ከሶስተኛ ወገን ተፅዕኖ ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ ማከናወን፣

### 6.1.6 የድንበር አከባቢዎች እና ድንበር-ተሻጋሪ የተፈጥሮ ሀብቶች

ኢትዮጵያ ከሰባት አጎራባች አገሮች ማለትም ኤርትራ ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳንና ሱዳን ጋር ትዋሰናለች፣ እነዚህ አገራት ጋር የድንበር ጉዳዮችን በአለም አቀፍ መርህ መሰረት የድንበሮቿ ምልከታ በማኖር እና በማካለል ረገድ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መቋጨት የሚገባቸው ስራዎች አሉ። በዚህ ረገድ የአለም አቀፍ ድንበሮቻችንን የሚወክሉ ህጋዊ ሰነዶች ተከትሎ በመልካም ጉርብትናና ትብብር ስራዎችን ለማጠናቀቅ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

የአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች ድንበር-ተሻጋሪ ወንዞችና ማዕድናት የመሳሰሉትን የወል የተፈጥሮ ሀብቶችን ይጋራሉ። ሃገሪቱ እነዚህን ሃብቶች በጋራ ለማልማትና ፍትሀዊ የወል ተጠቃሚነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተባብሮ ፍሬያማ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ይህንን ከግብ ለማድረስም ኢትዮጵያ የህግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን በማዳበርና በስራ ላይ በማዋል የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችን ታጠናክራለች። ከሁሉም የጎረቤት አገሮች ጋር ሀገሪቱ የምትጋራቸውን ድንበሮች በጥንቃቄና በመግባባት ማካለልና በትብብር ማልማት ያሰፈልጋል። እንዲሁም ከየሀገራቱ ጋር በስምምነት የተቋቋሙ የድንበር ኮሚሽኖች በየወቅቱ እየተሰበሰቡ በድንበርና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በቋሚነት እየመከሩ በድንበር ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን እየፈቱ የጋራ ልማትን እንድያጠናክሩ ያልተቆጠበ ጥረት ይደረጋል።

## 6.2 ታላላቅ ሀይቆች አካባቢ

የታላላቅ ሀይቆች በመባል የሚታወቀው አካባቢ ለኢትዮጵያ የሩቅ ጎረቤት ሲሆን በአፍሪካ ማዕከል የሚገኝ በተፈጥሮ ሀብት እጅግ የበለፀገ እና በዚህም ምክንያት የብዙ ዓለም አቀፍ ተዋንያንን (መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ) ትኩረት የሳበ ቀጠና ነው። ቀጠናው ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ግጭት ያልተለየው ካባቢ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ተስፋ ሰጪ መረጋጋትና የልማት ተስፋ ማሳየት ጀምራል።

ኢትዮጵያ ከዚህ አካባቢ ጋር ያላት ግንኙነት ታሪካዊ የሆነና በተለይም በኮንጎ የተ.መ.ድ የሰላም ማስከበር ጥላ ስር ተሳትፎ በማድረግ ረገድ ቀዳሚ ሃገር ናት። አካባቢው በግጭት እየታመሰ ሲሄድም ኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን ያለመታከት በአፍሪካ ህብረት ማዕቀፍ በሚካሄዱ ድርድሮችና በተለይም በሩዋንዳና ቡሩንዲ የሰላም ማስከበር ሂደቶች ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆናለች። እንደሚታወቀው የአካባቢው አገሮች የላይኛው የናይል ተፋሰስ አገሮች እንደመሆናቸው ኢትዮጵያ በትብብሩ ማዕቀፍ በህብረት መስራት ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዚህ አካባቢ በየጊዜው በሚከሰቱ ግጭቶች ሳይስተጓጎል ያለማቋረጥ ቀጠናውን ከአፍሪካና ከሌላው ዓለም ጋር የማገናኘት ተልዕኮውን ቀጥሏል። ኢትዮጵያ ከታላላቅ ሀይቆች አካባቢ ጋር የሚኖራት ግንኙነት በአፍሪካ የጋራ ገበያ ስምምነት እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመር እየታገዘ ወደ ዳበረ የኢኮኖሚና የንግድ ትስስር እንዲሸጋገር የሚተገበር ይሆናል። በተጨማሪም የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ህጋዊ ሥነ-ስርዓቱን አሟልቶ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ለማድረግ ተገቢው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ይከናወናል። የቀጠናው ሰላምና መረጋጋት እንዳይናጋ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት እና በተ.መ. ድ. አማካይነት አስፈላጊውን ድጋፍ ታደርጋለች።

## 6.3 ድንበር ተሻጋሪ ሀብቶችና የአባይ ተፋሰስ

የድንበር ተሻጋሪ ሀብቶች አጠቃቀም በትብብርና በመግባባት፤ በጋራ ተጠቃሚነት፤ በመተማመን፤ በመተሳሰብና ተግባራዊ በሆኑ የልምድ አሠራሮችና በዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል። ኢትዮጵያ በጂዖግራፊያዊ አቀማመጧ የበርካታ የታወቁ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ማለትም የዓባይ፤ የባሮ አኮቦ/ሶባት፤ ተከዜ/አትበራ ድንደር፤ ራሃድ፡ መረብ/ጋሽ፡ አዋ፤ ዋቤ ሸበሌ፤ ገናሌ/ዳዋ መነሻ በመሆኗ ሀገሪቷን በዚህ ረገድ እጅግ የታደለች አድርጓታል። ሀገሪቱ የድንበር

ተሻጋሪ የውሃ ሀብቶች አጠቃቀም ከውሃ ተጋሪ ጐረቤት ሀገሮች ጋር ፍትሐዊ፤ ሚዛናዊና ጉልህ ጉዳት በማያስከትል አግባብ የሚከናወን ይሆናል። ሀገሪቱ የናይል ተፋሰስ ትብብር ጅማሮን ለማጠናከርና ለማጐልበት ሁሉንም የተፋሰስ ሃገራት በሚያካትት መልኩ በመስራት ላይ ትገኛለች።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ በናይል ተፋሰስ ሀገራት የተፈረመው የትብብር ማእቀፍ ስምምነት ወደ ተግባር እንዲሸጋገር በትኩረት ትሰራለች። የትብብር ማዕቀፉ ወደ ተግባር እንዲሸጋገርና የውሃ አጠቃቀምና አመራር በተጨማሪ የአፍሪካ ቀንድና የታላላቅ ሀይቆች አካባቢን የማስተባበርና የማቀራረብ ውጤት ትሩፋት እንዲኖረው ጥረት ታደርጋለች። ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ገና ሲታሰብ ጀምሮ ከላይ የተጠቀሱትን መርሆዎች መሰረት በማድረግና የተፋሰሱን አገሮች ጥቅም በማይጎዳ መልኩ ተጠንቶ የተጀመረ ከመሆኑም በላይ ግድቡ የጋራ ጥቅምና ቀጠናዊ ትስስርን የሚያጠናክር በመሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ሃብቶች በፍትሐዊነት እንዲሁም ጉልህ ጉዳት ባለማድረስ የሚሉትን የአጠቃቀም መርሆዎች መሰረት በማድረግ የውሃ ሃብቶቿን የመጠቀም ፖሊሲዋን ተግባራዊ ታደርጋለች።

## 6.3 የአፍሪካ ሀገራትና አፍሪካ ህብረት

ኢትዮጵያ በፀረ- ቅኝ አገዛዝ እና ፀረ-አፓርታይድ ትግል ውስጥ ለአፍሪካ ነፃነት ግንባር ቀደም ሚና ተጫውታለች። የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የአፍሪካ ህብረት መስራች እና የአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ እንዲያገኙ የበኩሏን ጥረት አድርጋለች። ይህም በተከታታይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፤ በተለያዩ መድረኮች የአፍሪካን ተሰሚነት እና ተፅዕኖ ፈጣሪነት ማሳደግ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል።

### 6.3.1 የአፍሪካ አገራት

አፍሪካ የዲፕሎማሲያችም ማዕከል ነው። የኢትዮጵያ የወደፊት የእድገት ጉዞ ከአህጉሩ አገራት ጋር የተሳሰረ ነው። ኢትዮጵያ በፓን አፍሪካን ጽንሰ ኃሳብ በአህጉሩ የተለያዩ የፖለቲካ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት በማሳተፍ የበኩሏ ሚና ተጫውታለች። በሰላምና ፀጥታ ረገድ የጋራ ደህንነት ጽንሰ ሃሳብን በመያዝ የምናካሂደው የውጭ ግንኙነት ለአፍሪካ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው።በተጨማሪም አህጉሩ በንግድ ለማስተሳሰር የአፍሪካ የጋራ የንግድ ቀጠና ስምምነት የንግድ

ተወዳዳሪነትና አቅም ብሎም ከአገራት ጋር የሚኖር ግንኙነት በማጠናከር ተጠቃሚነታችን ለማረጋገጥ ትኩረት ይሰጠዋል።

አገራችን ከአፍሪካ አገራት ጋር ያላትን የሁለትዮሽ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር በትኩረት ትሰራለች። ከአገራቱ ጋር በንግድ፤ በኢንቨስትመንት እና በቱሪዝም መስክ የበለጠ ትስስር እንዲኖር ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያላትን የውክልና አድማስ በማስፋት ለራሷና ለአህጉሩ ሀገሮች እድገትና ዘላቂ ልማት እውን መሆን ከሚመለከታቸው ሁኩ ጋር በትብብር ጥረት ታደርጋለች። የአህጉሪቱ ዕድገትና ብልጽግና ከሰላምና መረጋጋት ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያለው በመሆኑ የአፍሪካ አገሮች ለአህጉራችን ብሎም ለዓለም-አቀፍ ሰላምና ፀጥታ የሚያደርጉትን ጥረት አጠናክረው እንዲቀጥሉ ግንባር-ቀደም ሚና መጫወት ያስፈልጋል።

ዜጐች በሚኖሩባቸው የአፍሪካ ሀገራት መብታቸው እንዲጠበቅ የሚያስችሉ የሁለትዮሽና ዘርፈ-ብዙ ስምምነቶችን ማድረግ በተለይም ፍልሰት ሕጋዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ የህዝብ- ለህዝብ ግንኙነቶችን በማጠናከር፤ የኢኮኖሚ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ትስስር ማሳደግ ያስፈልጋል። ሀገሪቱ ለአፍሪካ ሀገራት ዜጎች የሰጠችውን የመዳረሻ ቪዛ ዕድልንና ተመሳሳይ እርምጃዎችን በመውሰድ ለአህጉሩ አንድነትና ትስስር የበኩልዋን አስተዋጽኦ ታደርጋለች። የአፍሪካ ነጻ ገበያ ስምምነት ተግባራዊነትና ከዕድሉ ለመጠቀም የሚያስችሉ መንገዶችን ለመቀየስ በትኩረት ይሰራል።

### 6.3.2 የአፍሪካ ሕብረት

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው የአለም ጥቁር ህዝቦች ዘንድ እንደ ነጻነት ተምሳሌትነትና ተስፋ ስትቆጠር ኖራለች። ከኢትዮጵያ ስም ጋር የተያያዙ በርካታ የፖለቲካና የሲቪል ንቅናቄዎች በተለይ በአሜሪካና፤ በካሪቢያን አካባቢ ተፈጥረው እንደነበር በታሪክ የተመዘገበ ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ለተካሄዱ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግሎች ዙሪያ መለስ ድጋፍ በመስጠትም ትታወቃለች። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እ.አ.አ በ1963 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንዲመሰረት ሀገሪቱ የተለያዩ አቋሞችን በማቀራረብ ቁልፍ ሚና መጫወቷ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። በዚህ ረገድ የሀገሪቱ መሪዎች በአመራር ዘይቤያቸው ቢለያዮም በአፍሪካ ጉዳዩች ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ሲያራምዱ ይታወቃሉ።። ስለሆነም የሀገሪቱ ዲኘሎማሲ ጥብቅ አፍሪካዊ መሠረት ይዞ ሲካሄድ ቆይቷል።ኢትየጵያ በተባበሩት መንግስታት ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት ጥላ ስር ያሰማራችው ሰላም አስከባሪ ሃይል በቁጥር ትልቁ ሲሆን ሙሉ በሙሉ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ የተሰማራና ለአፍሪካ ሰላም ወደር የሌለው አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሃይል ሆኗል።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በኋላም የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ አገራችን እንድታስተናግድ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን የሰጡን ታላቅ አደራና ሃላፊነት በብቃት ለመወጣት ተችሏል። ስለሆነም ሀገሪቱ የአፍሪካን የጋራ ጥቅም በታማኝነት በማራመድ ረገድ ያለማቋረጥ የተከተለችውን ፖሊሲ የወቅቱን የአህጉሪቱን እውነታ መሰረት ባደረገ አግባብ አጠናክራ ትቀጥላለች።

በዚህ ረገድ አፍሪካን ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት የተደረገው ትግል ከተገባደደ በኋላ አህጉሪቱን ከድህነት፤ ከግጭትና ኋላቀርነት ለማውጣት በሚካሄደው ትግል ተገቢውን ሚናችንን ለመጫወት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች በስራ ላይ ይውላሉ።

1. በአፍሪካ ህብረት መመስረቻ ጉባኤ የፀደቀውን የህብረቱን መመስረቻ ሰነድ እና ዓላማዎች ለማክበርና ለማስከበር ጥረት ማድረግ፣
2. በተለያዩ የህብረቱ መድረኮች በየደረጃው በመሳተፍ፤ የኢትዮጵያ ብሎም የአህጉሩን ሰላምና ጥቅም ማስጠበቅ፤

3. ህብረቱ የአፍሪካን ሰላምና ፀጥታ በማስጠበቅ ረገድ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ሀገራቱ የሚጠበቅባትን እገዛ ማድረግ፣

4. በአፍሪካ የመልካም አስተዳደር የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታና የሰብዓዊ መብት አያያዝ መሻሻል እንዲችል ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት መንግስታት ጋር በትብብር በመስራት ግንባር ቀደም ሚና እንድትጫወት ማስቻል፣

5. የአፍሪካ ህብረት የነደፈውን አጀንዳ 2063 እና ከዚሁ ጋር የተያያዙት መሪ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ከሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ጋር መስራት።

6. ህብረቱ ከሌሎች ክልላዊ ቀጠናዎች፤ አህጉራት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በሚኖረው ግንኙነት የአፍሪካን ጥቅም ማስጠበቅ፤ የህብረቱ አባል ሀገራት በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ ድምፅ እንዲያስተጋቡና አብረው እንዲቆሙ ማትጋት፣

7. የአፍሪካን አህጉር የኢኮኖሚ ትስስር ለማፋጠን በቅርቡ የፀደቀውን አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነትን ተግባራዊነት ማረጋገጥ፤

8. የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን እና ሌሎች ተቋማት የተጣለባቸውን ሃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አቅም እንዲያዳብሩ በሚቻለው ሁሉ መርዳት፣

9. የአፍሪካ ህብረትና ሌሎች መድረኮችን በመጠቀም የአፍሪካን ባህል፤ ታሪክ፣ የተፈጥሮ ሀብት በዓለም ዙሪያ እንዲታወቅ ማድረግ፣

10. ኢትዮጵያ እንደ አፍሪካ ህብረት ኮሚሽን መቀመጫነቷ ለኮሚሽኑ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣ የአስተናጋጅ ሃገር ሃላፊነትን መወጣትና በአስተናጋጅነት ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ማጎልበት፣

11. በኮሚሽኑ እና በህብረቱ የተለያዩ አካላት የሚያገለግሉ ኢትዮጵያዊያንን መብት ማስጠበቅ፤ ኢትዮጵያውያን በአፍሪካ ህብረት የተለያዩ አካላት ውስጥ እንዲወከሉ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር በመመካከር በትብብር መስራት፣

## 6.4 መካከለኛው ምስራቅ

ይህ ኣከባቢ በባህል በሃይማኖት በታሪክና በአካባቢያዊ ቅርበት የኢትዮጲያ የሰላም የፖለቲካ እና የማህበራዊ ጉዳዩች ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ የአለም ክፍል ነው። በተጨማሪም በተፈጥሮ ሃብት በተለይም የነዳጅ ሀብት ሽያጭ ሀብት ያካበቱ ለኢኮኖሚያዊ ትስስር ረገድም ለኢንቨስትመንት ምንጭ ለንግድና ቱሪዝም መስፋፋት አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉ አገራት የሚገኙበት ከባቢ ነው።

ከሰላም እና ፀጥታ እና ከውጪ ግንኙነት አኳያ በመካከለኛው ምስራቅ አከባቢና በሃገራቱ መካከል የሚፈጠር ክስተት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ተጸእኖ ያለው መሆኑን ኢትዮጵያ ትገነዘባለች። ስለሆነም ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ጋር ሀገሪቱ የሚኖራት ግንኙነት ዘላቂ ጥቅሟን የሚያስከብር፣ የዓለም አቀፍ ህግና መርህን የተከተለ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል።

ከቀይ ባህር ተጠቃሚ መሆን ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ነው። በቀይ ባህር አከባቢ የሚታዩ ክስተቶች ከሃገሪቱ ብሄራዊ ጥቅም ጋር በቀጥታ የሚያያዙ በመሆናቸው፣ እንዲሁም የቀይ ባህርና የኤደን ባህረሰላጤ ከአፍሪካ ቀንድ ሃገራት ጋራ ካላቸው ትስስርና ጠቀሜታ አኳያ ኢትዮጵያ በተጠቀሱት አከባቢያዊ ጉዳዮች የሚኖራትን ሚና ከሌሎች የሚመለከታቸው አገሮች ጋር ለመሥራት በትብብር ትንቀሳቀሳለች። ስለሆነም በቀይ ባህር ዙሪያ ሀገሪቱ ያላትን ዘላቂ ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በቀይ ባህር ዙሪያ የጋራ ጥቅም ካላቸው ሀገሮች ጋር በጋራ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን የባለብዙ ወገን መድረክ እና የትበብር ማዕቀፍ ለመፍጠር አባል የመሆን ጉዳይ ትኩረት በመስጠት ይከናወናል።

የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ለኢትዮጵያዊያን የስራ ምንጭ በመሆን መዳረሻ ስለሆኑ ወደነዚህ ሀገራት የሚጓዙ ዜጎች የህግ ከለላ እንዲኖራቸውና በስራ ሲሰማሩም በዓለም-አቀፍ የሥራ ስምምነት ህግ ድንጋጌ ህግ መሠረት መብታቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ እና በሚያገኙት ፋይናንስ እና ሀብት እራሳቸውን ጠቅመው ሀገር እንዲጠቅሙ የሚያስችሉ ስምምነቶችን ከእያንዳንዱ ሀገር ጋር ማድረግ ይገባል። ከመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ጋር ሀገሪቱ ባላት ግንኙነት ልትከተለው የሚገባው የፖሊሲ አቅጣጫ በዋነኛነት የሁለትዮሽ ግንኙነትን ተጠቅሞ ከነዚህ አገሮች ጋር የተጠናከረ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት፤ በተለይም ንግድ፤ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ላይ ያተኮረ ግንኙነትን ለማስፈን በትጋት መሥራት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ጋር የሚኖራት ግንኙነት

የኢትዮጵያን ዘላቂ ብሄራዊ ጥቅም ባስጠበቀ እና ሃገሪቱን ለኢኮኖሚ እና ለማህበራዊ ልማት የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ አጠቃላይ የንግድ እና ኢኮኖሚ ሂደት ተጠቃሚ እንድትሆን በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል።

## 6.5 የአውሮፓ ህብረት

የአውሮፓ ህብረት 28 ሃገራትን ያቀፈ ወደ ከፍተኛ የገበያ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ህብረት የተሸጋገረ ስብስብ ነው። ሕብረቱ በዓለም የኢኮኖሚ፣ የንግድና የፖለቲካ ትስስር በዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መስክ ዋነኛ ተዋናይ የሆነና ከታዳጊ አገራት ጋር የትብበር ስምምነት መመስረት የቻለ አካል ነው። በልማት ትብብር ረገድ ህብረቱ ከአፍሪካ ፣ ከካሪቢያንና ፓስፊክ (አ.ካ.ፓ) አገራት ጋር የተፈራረማቸው የሎሜ(እ.ኤ.አ 1975) እና የኮቶኑ(እ.ኤ.አ 2000) ስምምነቶች የግንኙነትና የትብብር መሰረቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ሕብረት ጋር ያላት ግንኙነት የተመሰረተው የሎሜ ስምምነት ፈራሚ በመሆኗ ነው። ሀገሪቱ የምትከተለውን ድህነት-ተኮር ፖሊሲና የልማት አቅጣጫ ከሕብረቱ የልማት እርዳታ ፖሊሲ ጋር ባመዛኙ የተጣጣመ በመሆኑና በአካባቢያችን የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት የምታደርገውን ያለሰለሰ ጥረት እንዲሁም በአከባቢው ሀገራት ውስጥ ያላትን ተሰሚነት ታሳቢ በማድረግ ህብረቱ ቁሳዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ያስመዘገበችውን የኢኮኖሚ እድገትና በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት ለማምጣት የምትጫወተውን ሚና ተከትሎ ከህብረቱ ጋር የነበራትን ግንኙነት ወደ ላቀ ምዕራፍ የሚያሸጋግር ስምምነት ተፈርሟል።።

### 6.5.1 ኢኮኖሚ ትብብር

ኢትዮጵያ ከህብረቱ የልማት ትብብር አጋሮች መካከል ግምባር ቀደም ተጠቃሽ ናት። በዚህም ምክንያት ከሎሜ እና ከኮቶኑ የትብብር ስምምነቶች በመጠቀም የተለያዩ የፋይናንስ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ አግኝታለች። በዚህም የኮቶኑ የአጋርነት ስምምነት ድንጋጌን መሰረት አድርጎ በተዘጋጀው የሀገራዊ እስትራቴጂ ፕሮግራሞች መሰረትም ለድህነት ቅነሳ፣ ለአስቸኳይ ጊዜ ርዳታ፣

ለብድር ቅነሳና ለውጭ ንግድ መዋዠቅ ማካካሻና በመሳሰሉት ጉዳዮች የተለያዩ ድጋፎችን አግኝታለች።

በተጨማሪም ሕብረቱ በልማት ወደ ኃላ ለቀሩ አገሮች በሰጠው ከጦር መሳሪያ ለሆነ ውጭ(EBA) ሁሉን-አቀፍ የድጋፍ እድል ማንኛውንም ምርት ወደ አውሮፓ ገበያ ያለቀረጥ ለማቅረብ በተመቻቸው አግባብ ሀገሪቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ስትሆን እነዚህን ወደ አውሮፓ የምታቀርባቸውን የወጪ ምርቶች በአይነት፣ በጥራትና ብዛት በመላክ እድሉ ይበልጥ ለመጠቀም እንዲቻል ትኩረት በመስጠት መስራት ይገባል።

የአውሮፓ ህብረት ከአንድ ሀገር በላይ የሆኑ ሀገራት ተጠቃሚ የሚሆኑበትና የአካባቢያዊ ትስስርን የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችን ለማስፈፀሚያ ካዘጋጀው የአካባቢያዊ አመልካች ፕሮግራም ሀገሪቱ ተጠቃሚ የምትሆንበትን መንገድ ለማመቻቸት የተቀናጀ ጥረት ማድግ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ተግባራዊ እንዲሆን የሚጠበቀው ስራ ሀገሪቱ ከቀየሰችው የቀጠና የኢኮኖሚ ትስስር ጋር ተቀናጅቶ የሚከናወን ይሆናል።

## 6.5.2 ፍልሰትና ስደተኝነት

ፍልሰት በተለይም ሕገ-ወጥ ስደት በአለም አቀፍ ደረጃ በየጊዜው እያደገ በመምጣቱ በስደት መነሻ፣ መተላለፊያና መዳረሻ አገራት መካከል የችግሩን ደረጃ የሚመጥን ትብብር ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል። በኢትዮጵያና በአውሮፓ ህብረት መካከል ባለው ግንኙነት ማዕቀፍ ውስጥ የፍልሰትና ስደተኝነት ጉዳይ ዋነኛው እየሆነ መጥቷል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የቫሌታ የድርጊት መርሃ-ግብር እና በሁለትዮሽ ግንኙነት ደረጃም የፍልሰትና የሰዎች ዝውውር የጋራ አጀንዳ ስምምነት ፈርማለች። በዚህም ፍልሰትና ህገ-ወጥ ስደተኝነት የሚያስከትሏቸውን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም የአውሮፓ ህብረት ካቀረበው የመዋእለ ነዋይ ድጋፍ ተጠቃሚ ሆናለች። በዚህ መስክ ለስደተኞች የስራ እድል ለመፍጠር የኢንዱስትሪ ፓርክ ገንብቶ ስራ ላይ ማዋል በሚል የተጀመረው ጥረትና እንቅስቃሴ ትኩረት ተሰጥቶት በይበልጥ መቀጠል የሚገባው ነው።

### 6.5.3 በሰላምና ፀጥታ መስክ መተባበር

ህብረቱ በኢትዮጵያ የሚካሄዱትን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፕሮግራሞችን (የሰብዓዊ መብት አያያዝ፣ የሚዲያና ፕሬስ ነፃነትና የሲቪክ ማህበራት ተሳትፎ) ለማጠናከር በሚደረገው እንቅስቃሴ አጋዥ ሚና እንዲጫወት የጋር ምክክሮችና ውይይቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ሀገራቱ የአፍሪካ ቀንድ የተረጋጋ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አከባቢ እንዲሆን የምታከናውናቸው የዲፕሎማሲ ጥረቶች ድጋፍ እንዲያገኙና ቀጠናዊ ድርጅቶችም የማስፈፀም አቅም እንዲኖራቸው በህብረቱ የተጀመሩት ምክክሮችና ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠልም ይገባል። በአጠቃላይ ሃገራቱ ከአውሮፓ ህብረት ጋር ያላትን ዘርፈ-ብዙ ግንኙነት ለማጠናከርና ወደ ስትራቴጂካዊ አጋርነት ለማሳደግ በትኩረት ትሠራለች።

## 6.6 የአውሮፓ ሃገራት

ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ህብረትና የህብረቱ አባል ካልሆኑ ሃገራት ጋር ረጂም ጊዜ ያስቆጠረ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አላት። በተለይም ከአንዳንድ አገራት ጋር ያላት ግንኙነት ስትራቴጂካዊና በከፍተኛ ደረጃ እየተጠናከረ የመጣና ሁሉን-አቀፍ ሊባል የሚችል እንድምታ ያለው ነው። የአውሮፓ ሃገራት በየጊዜው እየተሻሻለ የመጣውን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ተከትሎ ኢትዮጵያ ለነደፈቻቸው ድህነት-ተኮር የልማት ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚውል ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍን ጨምሮ፣ የብድርና የተለያየ የቴክኒክ ድጋፍ እያደረጉ ሲሆን ይህ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መትጋት ያስፈልጋል።

### 6.6.1 ንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም

ለሀገሪቱ የወጪ ምርቶች የገበያ እድል ለማስገኘት በአውሮፓ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በጥራት ማምረት ላይ በይበልጥ መስራት የሚገባ ሲሆን ፣ ይህንኑ ለማሳካት ተፅእኖ ፈጣሪ የሆኑ ባለሃብቶችንና ኩባንያዎችን መልምሎ ወደ ስራ ዋነኛው ነው። አሁን ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሸጋገር የገበያ ዕድሎችን በጥናት ላይ በመመሥረት ማስፋት ይገባል።ከአውሮፓ አገራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቱሪስቶችን በመሳብ በሀገር ውስጥ ያሉትን የቱሪስት መስህቦች እንዲጎበኙና ለኢኮኖሚዋ ደጋፊ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ማበረታታት ያስፈልጋል።

## 6.6.2 ሰላምና ደህንነት

በተ.መ.ድ. የፀጥታ ምክር ቤት ቋሚ አባላት ከሆኑትና የህብረቱ አባል ካልሆኑ የአውሮፓ ሃገራት ጋር በአፍሪካ የሰላምና የፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ከኢትዮጵያ ጋር በመተባበርና በመመካከር እንዲሰሩ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። ሀገራቱ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ለምታከናውናቸው የሰላምና ደህንነት ስራዎች የዲፕሎማሲና የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ አሁን ያለውን መልካም ግንኙነት አጠናክሮ ለማስቀጠል በትብብር ይሰራል።

## 6.6.3 ዓለምአቀፍ ጉዳዮች

ኢትዮጵያ የህብረቱ አባል ካልሆኑ የአውሮፓ አገራት በዓለምአቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ የምትሠራባቸው ጠንካራ መሰረት ያላቸው የትብብር መስኮች አሉ። የተ.መ.ድ. የ2030 የዘላቂ የልማት ግቦችን ለመተግበር ሀገሪቱ ለምታከናውናቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የአውሮፓ አገራት የሚሰጡትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥረት ይደረጋል።

## 6.7 የሰሜንና ደቡብ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች

### 6.7.1 ሰሜን አሜሪካ

የሰሜን አሜሪካ ክፍለ-አህጉር በአለም የሃብት መጠን ከፍተኛውን ደረጃ የያዙ ተጽእኖ ፈጣሪ የሆኑ የቡድን ሰባት አባላት ያሉበት ክፍለ አለም ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መቀመጫ እና የዓለም የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች የሚወሰንበት አካባቢም ነው። ኢትዮጵያ ከአገራቱ ጋር ያላትን ግንኙነት ታሪካዊና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። በአካባቢው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት አካባቢ ከመሆኑ አንፃር ግንኙነቱ እጅግ አስፈላጊ ተደርጎ ይወሰዳል።

#### 6.7.1.1 ሰላምና ደህንነት፤ ሽርተኝነትን መዋጋት

ከአሜሪካና ካናዳ ጋር የአከባቢያዊ ሰላምና ፀጥታን በማስጠበቅ ሽብርተኝነት፣ ፅንፈኝነትና አክራሪነት በጋራ በመከላከልና መዋጋት ረገድ ሃገራቱ እያበረከቱት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ከሃገራቱ ጋር የምታደረገውን ትብብር አጠናክራ ትቀጥላለች። አገራቱ በአለምአቀፍ ተቋማት ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ይህንኑ ከግንዛቤ በማስገባት በአለምአቀፍ አበይት ጉዳዮች ዙሪያ ኢትዮጵያ ለጋራ ተጠቀሚነት ከነዚህ ሃገራት ጋር እየተመካከረች ትሰራለች።

#### 6.7.1.2 ኢኮኖሚ ትብብር

ኢትዮጵያ ከነዚህ ሃገራት ለኢኮኖሚ ልማት አጋዥ የሚሆኑ የፋይናንስ፣ የቴክኒክና ሰብአዊ ድጋፍ ለማግኘትና በሀገሪቱ መልካም አስተዳደር የማስፈንና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትረት ዙርያ ትተባበራለች። ከሃገራቱ የተለያዩ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፎች የምታገኝ ሲሆን ይህንኑ በቀጣይም በአይነትና በብዛት እንዲጨምር ጥረት ይደረጋል።

#### 6.7.1.3 ንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም

የሰሜን አሜሪካ ሃገሮች ለኢትዮጵያ ምርቶች ሰፊ የገበያ ዕድል የሚሰጡ ከመሆኑ አንፃር ፣ ያሉትን ዕድሎች ለምሳሌ እንደ አጎዋ (AGOA) ያሉትን አሟጦ ለመጠቀም ጥረት ይደረጋል። ከአገራቱ ጋር

ያለውን የኢንቨስትመንትና የሃብት አቅም አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል በኢትዮጵያ የሚታዩትን የኢንቨስትመንት ማነቆዎች በመፍታት ፍሰቱ እንዲጨምር ይሰራል። ከሰሜን አሜሪካ የሚነሱ ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ቱሪስቶች ወደ ሀገሪቱ በመሣብ ከቱሪዝም ኢንዱስትሪው የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ የውጭ ግንኙነት ፓሊሲው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

#### 6.7.1.4 በአካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ትውልደ-ኢትዮጵያውያን

በአከባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ከሃገራቱ ጋር የምታደርገውን ሁለገብ የሁለትዮሽ ግንኙነት ከማጠናከር አኳያ የድርሻቸውን እንዲወጡ ማበረታት ይገባል።በተለይም በተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩና ለሀገራቱ ግንኙነት መጠናከር አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ ታምኖበታል።

### 6.7.2 የደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን አገሮች

ኢትዮጵያ ከደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን አገሮች ጋር በደም የተሳሰረ ታሪካዊ ግንኙነት ያላትና በአለምአቀፍ መድረኮች ላይ ሰፊ የጋራ አጀንዳዎች በመቅረጽ በትብብር የመስራት መልካም ልምድ አላት። ሀገሪቱ በአለምአቀፍ መድረኮች የምታካሂደውን እንቅስቃሴና የምታራምድውን አቋም በመደገፍ ረገድ ትልቅ ሚና እያበረከቱ ሲሆን ይህንኑ ታሪካዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ያስፈልጋል። በዚህም መሰረት ከሃገራቱ ጋር፡-

- ❖ የቴክኒክ ድጋፍና ተስማሚ ቴክኖሎጂ ሽግግር ማስገኘትን ማዕከል ያደረገ ግንኙነት መመስረትና የተጀመረውንም ማጠናከር፣
- ❖ አብዛኞቹ ሃገራት የደቡብ- ደቡብ ማዕቀፍ አባል ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በአለምአቀፍ መድረኮች የጋራ አቋም በማራመድ አጋርነትን ማጠናከር፣
- ❖ ከካሪቢያን አገራት ጋር ሀገሪቱ ያላትን ትስስር በማጠናከር በአለምአቀፍ መድረኮች ሀገሪቱ ለምታደርገው ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ አጋር እንዲሆኑ ማስቻል፣
- ❖ የካሪቢያን አገራት በቱሪዝም መስክ ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ መጠቀም የሚያስችል ግንኙነት በመፍጠር ለቱሪዝም ዘርፍ መጠናከር በትጋት መስራት፣

## 6.8 እስያ-ፓስፊክ

የእስያ አህጉር ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ታላቅ የኢኮኖሚ እድገትና እመርታ ያሳየ ክፍለ ዓለም ሲሆን ያቀፋቸው ሀገራት ሕዝቦቻቸው ወደ መካከለኛ ገቢ ለማድረስ የተሳካ ጉዞ አድርገዋል። በመሆኑ በተለያየ የዓለም ክፍል በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ለነበሩ አገሮች አርአያ ለመሆን የቻሉ ናቸው። የእስያ አገሮች እድገት ለአፍሪካ የኢንቨስትመንት ምንጭና የገበያ እድል እንዲፈጠር ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ከእስያ አገሮች ጋር በፈጠረችው ግንኙነት ጉልህ በሆነ መልኩ ተጠቃሚ ሆናለች። ይህ አህጉር  ለኢትዮጵያ የእድገት ደረጃ ተስማሚ ቴክኖሎጂ የሚገኝበት፣ ከፍተኛ የቱሪስት ምንጭ የሆነ እንዲሁም በሰላምና በደህንነት ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመስራት ሠፊ ዕድል መኖሩን ያካትታል።

የእስያ አገሮች ከአፍሪካ አገራት ጋር የሚሰሩበት ማዕቀፍ ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ ነው ናቸው። ስለሆነም በነዚህ ተቋማዊ ማዕቀፎች ውስጥ በጋራ በመስራት የሚገኙ ጥቅሞችን መሳብ አስፈላጊ ይሆናል። የነዚህ ሃገራት ትኩረት በመንገድ፣ በባቡር፣ በወደብ፣ በኢነርጂ ወዘተ መሰረተ ልማቶች ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ በአፍሪካ ውስጥ ለሚፈጠረው የእርስ በእርስ ትስስር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

ሀገሪቱ ከእስያ አገሮች ጋር ባላት ግንኙነት ልትከተል የሚገባው ፓሊሲ በዋነኛነት በዘመናት ያዳበረችውን የሁለትዮሽ የግንኙነት መንገድ ተጠቅማ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን፣ የኢንቨስትመንትና፣ የውጭ-ንግድ ገበያ የመሳሰሉትን ዕድሎች ወደ ሚቀጥለው የዕድገት ምዕራፍ ለመሸጋገር በሚያግዝ አግባብ ለመጠቀም መስራት ተገቢ ነው። ከሁለትዮሽ የትብብር መንገዶች በተጨማሪ ከአፍሪካ ጋር የተፈጠሩት የጋራ የትብብር መድረኮችን በመጠቀም ውጤታማ የደቡብ-ደቡብ ትብበር እንዲሰፋና እንዲጠናከር መሥራት ይገባል።

ከኢኮኖሚያዊ ትብብር ባሻገር ከእስያ አገሮች ጋር በዓለም አቀፍ ሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ላይ እንዲሁም በሽብርተኝነትና በማሪታይም ደህንነት ረገድ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኩልም ሆነ በሁለትዮሽ ደረጃ በትብብር ትሠራለች። ከመንግስት- ለመንግስት ግንኙነት ባሻገርም የህዝብ-ለህዝብ ግንኙነት እንዲስፋፋ የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት በንግድ ምክር ቤቶች፣ በትምህርት እድል፣ በምርምር ተቋማት የጋራ የምርምር ፕሮግራሞች በመቅረፅ

በተለይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ፣ በባህል ልውውጦች፣ በሚዲያ ትብብሮችና በሲቪል ማህበራት ግንኙነት እና በመሳሰሉት መስኮች ሀገሪቱ ያላትን ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የሚደረግ ትብብር በእስያ አገሮች ውስጥ የኢትዮጵያን ገፅታ በአዎንታዊነት ለማንፀባረቅ አይነተኛ የግንኙነት ዘርፍ ሆኖ እንዲያገለግል ጥረት ማድረግ ይገባል።

## 6.9 የባለ-ብዙ ወገን ግንኙነቶች

ኢትዮጵያ በአፍሪካ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለባለብዙ ወገን ግንኙነት መድረኮች ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ በማድረግ ትታወቃለች። በዓለም ማህበር በኋላም በተባበሩት መንግስታት እና በአፍሪካ ደረጃ (በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት) የጋራ የዓለም ፀጥታን በጋራ ለማረጋገጥ ብሎም የአፍሪካ ድምፅ በመሆን ለፀረ ቀኝ አገዛዝ ትግል አስተዋፅኦ አድርጋለች። ይህም ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የዘለቀ ለባለብዙ ወገን ግንኙነት ያላትን ቁርጠኝነት ያመላክታል። በታሪክ እንደታየው በዓለም አቀፍ ህግ የሚመራ ግንኙነትን የምትደግፍ ሲሆን እንደታዳጊ ሃገር የባለበዙ ወገን ግንኙነት ለዓለም አቀፍ ችግሮች መፍትሄ ለመሻት እና ለጋራ ልማት እና ብልፅግና አብሮ ለመስራት አማራጭ የሌለው መሆኑን ታምናለች። የዓለም አቀፍ የትብብር ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ፣ የዓለም አቀፍ ህግ የበላይነትን በማስከበርና በአገሮች መካከል ትብብርን በማጎልበት የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተኪ የሌለው ሚና ይጫወታሉ።

አሁን ካለንበት የዓለም ሁኔታ ለውጦች በተለይም በሃያላን አገሮች መካከል እየሰፋ የመጣው ውጥረት ለባለብዙ ወገን ግንኙነት ትብብር ፈተና ሆኗል። በተለይም በፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባላት መካከል የተፈጠረው የቀዝቃዛው ጦርነትን የሚያስታውስ ሁለት ጎራ መፈጠሩ የሰላምና የፀጥታ ጉዳዮችን (ትንሽ የሚባሉትንም ጨምሮ) ለመፍታት አስቸጋሪ ሁኔታን የፈጠረ ነው።

ከዚህም ባለፈ የባለብዙ ወገን ጉዳዮችን ወደ ጠበበ መድረክ በመውሰድ ተቋማት መጫወት የሚገባቸውን ሚና እንዳይጫወቱ እንቅፋት እየተፈጠረ ይገኛል። የባለብዙ-ወገን ግንኙነት ሌላው የጋጠመው ፈተና አገሮች ከዓለም አቀፍ ትብብር ይልቅ ለሃገር ውስጥ ጉዳዮች ያጋደለ ትኩረት መስጠታቸውና በዓለም አቀፍ ትብብር ላይ ያላቸው እምነት መቀነስ ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር የሚያደርጉትን የፋይናንስ ድጋፍ እንዲቀንሱ አድርጓል።

በዚህም ምክንያት እንደ ኢትዮጵያ ለሰላምና ፀጥታን ለማስፈን የሰላም አስከባሪ ሀይል የሚያሰማሩ አገሮች የሚያደርጉትን አስዋፅኦ እንዲሁም በአፍሪካ በተለይም በቀጠናው ያሉ ግጭጦች እንዲፈቱ የሚደረገውን ጥረት የሚያዳክም ሆኗል። የባለብዙ-ወገን ግንኙነት ለዓለም አቀፍ ችግሮች የጋራ መፍትሄ እና ሁሉንም ተጠቃሚ ለማድረግ መሰረታዊ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ያጋጠማትን  ፈተናዎች ለመቋቋም ከሌሎች ተመሳሳይ አቋም ካላቸው አገሮችና የባለብዙ ወገን ድርጅቶች ጋር ተባብራ ትሰራለች። ከዚህ አኳያ የአፍሪካ ህብረት መድረክን እንዲሁም አፍሪካ ከሌሎች አህጉራትና ተፅእኖ ፈጣሪ አገሮች ጋር ያላትን የጋራ መድረክ በመጠቀም የባለብዙ ወገን ግንኙነት እንዲጠናከርና የዓለም አቀፉ ህግ የበላይነት እንዲከበር የድርሻዋን ትጫወታለች። ሰላም ማስከበር ለግጭቶች መፈታት ካለው ጉልህ አስተዋፅኦ አኳያ የሚደረግለት የፋይናንስ ድጋፍ ሃላፊነቱን መወጣት በሚያስችለው መጠን እንዲሆን እና ለአፍሪካ ህብረት መር የሰላም አስከባሪ ተልዕኮ አስተማማኝና ዘላቂ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲደረግ ከሌሎች አገሮችና ተቋማት ጋር በትብብር ትንቀሳቀሳለች።

አሁን ካለው የዓለም የዓለም ሁኔታ ለውጦች በመነሳት በባለብዙ ወገን ግንኙነት መድረኮች በሚፈጠረው የሀያላን ሀገራት ሽኩቻ ወገንተኝነትን የማያንፀባርቅ አካሄድን በጥንቃቄ ግልፅነትን በተላበሰና ወጥነት ያለው አካሄድ በመከተል የሀገሪቷ ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብር ዓለም አቀፍ ህግን የተከተለ አቋም ታራምዳለች። በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዳጊ አገሮች ፍትሀዊ ድምጽ እንዲያገኙ የሚረዱ በይነ መንግስታዊ መድረኮች የተ.መ.ድ የ2030 ዕቅድ በማስፈፀም ረገድ የሚኖራቸውን የአጋርነት ሚና ትደግፋለች። በአፍሪካ ህብረት እና መሰል ተቋማት በተለይም ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና አውሮፓ ህብረት ጋር የሚደረግ ትብብር እንዲጠናከርና የአፍሪካ አገራትን እንዲሁም የቀጠናው ጥቅም እንዲከበር ጥረት ታደርጋለች። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዙሪያ ሊደረግ የታሰበው ለውጥ የአፍሪካን ጥቅም ባስከበር መልኩ እንዲካሄድ ኢትዮጵያ የአፍሪካን የጋራ አቋም ታራምዳለች። ከነባር እንዲሁም አዲስ ከተቋቋሙ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጋር የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና የልማት አቅጣጫን መሰረት በማድረግ ትብብርን በማቀላጠፍ ተጠቃሚ በምትሆንበት መንገድ ትሳተፋለች። ከተ.መ.ድ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ኤጀንሲዎች ጋር ያላትን ግንኙነት ጥቅሟን ባስከበረ መልኩ እንዲጠናከር ይደረጋል። በተጨማሪም

በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚኖረው የኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ እንዲያድግ በትኩረት ይሠራል።

# 7. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አፈፃፀም

## 7.1 አቅጣጫና አካሄድ

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት እና የዲፕሎማሲ ታሪክ እንደሚያሳየው አገራችን በዓለምአቀፍ መድረኮች ወጥ የሆነ አቋም ስታራምድ ቆይታለች። ይህንን ፖሊሲ ተቋማዊ በሆነ፤ በጥናትና ትንተና በተመሰረተ በቂ አቅምና ክህሎት በማዳበር እንዲሁም ሁኔታዎችን በመተንተን ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ጉድኝቶችን በመፍጠር ፖሊሲው ወጥ በሆነ መንገድ የማስፈፀም ሃላፊነት አለበት። የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ተለዋዋጭ በሆነ ዓለም-አቀፋዊ ሁኔታ ላይ የሚተገበር በመሆኑ በሚኒስትሩ የሚመራ የውጭ ግንኙነት ምክር ቤት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተቋቁሞ መንግስትንና ሚኒስቴር መ/ቤቱን በፖሊሲ ጉዳይ አዳዲስ የፖሊሲ ሃሣቦችን በማመንጨት እንዲያግዝና እንዲያማክር ይደረጋል።

ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚያገለግል የማስፈፀሚያ ሰነድ ወይንም ዝርዝር የሆነ የአፈፃፀም መመሪያ በሚኒስቴሩ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሆኖ ፖሊሲው ከሌሎች አገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታና በቅንጅት መተግበሩን ያረጋግጣል።

## 7.2 ተቋማዊ አሰራር

ተቋማዊ አሰራር ሲባል በዋናነት በዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም ሃላፊነትና ድርሻ ያላቸውን አካላት መለየት በዚህም መሰረት፡-

1. የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
2. የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
3. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
4. የመከላከያ ሚኒስቴር
5. የገንዘብ ሚኒስቴር

6. ሌሎች በአዋጅ ከውጭ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ሥራዎችን እንዲሰሩ በአዋጅ ኃላፊነት የተሰጠቸውና የሚመለከታቸው ሴክቴር መ/ቤቶች፣

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን ፖሊሲ ለማስፈጸም እንደአስፈላጊነቱ

1. ከምርምርና ስልጠና ተቋማት
2. ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውስጥ የስልጠናና ምርምር ተቋም
3. ከሌሎች የምርምርና የስልጠና ተቋሞች
4. ከዳያስፖራ ማህበራት
5. ከሲቪል ማህበራት
6. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
7. ከውጭ ግንኙነት ጉዳዮች አማካሪ ም/ቤት የሚከተሉት አካላት የሚያሳትፍ መሆን
   I. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀድሞ ባልደረቦች
   II. የግል ባለሀብቶች/ማህበር
   III. ታዋቂ ግለሰቦች
   IV. የዘርፉ ምሁራን ጋር በትብብር ይሠራል።

ፖሊሲው ሲጠናቀቅ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የማስፈፀምና ዝርዝር አደረጃጃት ደንብ ያዘጋጃል።

## 7.3 የፖሊሲ ጥናትና ትንተና

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የአገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም በሚያስከብር መልኩ በአፍሪካ ቀንድ በናይል ተፋሰስ ሀገሮች፤ በአፍሪካና በመካከለኛ ምስራቅ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት እና ተቀባይነት ባለው መልኩ የተቃኘ መሆን ይገባዋል። የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለረጅም አመታት እንዲያገለግል ታስቦ የሚቀረፅ ቢሆንም በየጊዜው የሚቀያየሩ ቀጠናዊ፤ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ትንተና በማድረግ እነዚህን ታሳቢ በማድረግና የፖሊሲ ማሻሻያ በማቅረብ የፖሊሲ አቅጣጫን ማስተካከል ያስፈልጋል።

በመሆኑም ይህንን ለማድረግና ለማሳካት የሚያስችል ተከታታይና ተቋማዊ አሰራርን የተከተለ፣ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ፣ በበቂ ጥናት፣ ትንተና እና የሴናርዮ ቀረፃ ስራዎች ላይ የተመሰረተ

የፖሊሲ ይዘትና አቅጣጫ መከተል ይገባል። ስለዚህም የሚኒስቴር መ/ቤቱና ሌሎች የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አስፈፃሚ አካላት የትንተናና ምርምር እንዲሁም ሲናርዮ ቀረፃ ስራዎችን በተቋማዊ መልኩ ማከናወንና በነዚህ ተቋማት መካከልም ቅንጅትና ትብብር እንዲፈጠር ማድረግ ያስፈልጋል።

## 7.4 ሥልጠና እና የአቅም ግንባታ

የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አፈጻጸም ውጤታማ ለማድረግ በየጊዜው ተከታታይና ቋሚ በሆነ የሥልጠናና አቅም ግንባታ ፕሮግራም የታገዘ ይሆናል። በዚሁ መሰረት በተቋማዊ የሰው ሃብት ልማትና አቅም ግንባታ ስራዎችን ላይ ማተኮር የሚገባ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ይዘረጋሉ። ለዚህም የሚሆን ከአዋጆችና ደንቦች ጋር የተጣጣመ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል ልማት ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል።

የዲፕሎማሲ ሥራን ሊያንቀሳቅስ የሚችል ሙያተኛ የሰው ሃይልን ያማከለ አደረጃጀትና የሥራ ስምሪት ተግባራዊ ይደረጋል። ከዚህ አንፃር የሚኒስቴሩ የዲፕሎማሲ ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም አቅም እንዲጠናከር ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ የሥልጠና ፕሮግራሞቻችንን በውጭ ሃገር በሚገኙ ሌሎች መሰል ተቋማትን ልምድና አሰራር ለመቅሰም በሚያስችል መልኩ የተቃኙ እንዲሆኑ ይሰራል። የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አፈፃፀም በይዘቱ በርካታ ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ እንደመሆኑ የተቋሙ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ባለድርሻ አካላትና ተቋማት ሊሳተፉ የሚችሉበትን መንገዶች በመቀየስ፤ በማቀናጀትና በማመቻቸት ተግባራዊ ይደረጋል። በተጨማሪም በሃገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ዜጎችን የጋራ የሆኑ ግንዛቤ እንዲይዙ በማድረግ ረገድና አጋዥ ሃይል ሆነው እንዲቆሙ ለማድረግ መስራት ተገቢ ነው።

የሚኒስቴሩ አቅም ከመገንባት አኳያ በዲፕሎማሲው መስክ በርካታ ልምድ ያካበቱ ነባር ባለሙያዎችን በማሰባሰብ ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ በተደራጀ መልኩ ማካፈል የሚችሉበትን አሰራር ለማስፈን በትኩረት ይሰራል።